የትንቢት መንፈስ ስጦታ አስፈላጊነት



The Need of the Spirit of Prophecy Gift

መግቢያ

ይህ ጽሁፉ የተዘጋጀበት ዓላማ

1. እውነተኛ ነብያትን እንዴት መለየት እንደምንችል ለማሳየት
2. ሀሰተኛ ነብያትን እንዴት መለየት እንደምንችል ለማሳየት
3. እግዚአብሔር በነብያት የሚጠቀምበትን መንገድ ለማሳየት
4. እግዚአብሔር የተጠቀመባቸውን ነብያት ማሳወቅ
5. ነብያት የሚናገሩባቸውን መንገዶች ማሳወቅ
6. እግዚአብሔር ነብያትን ተጠቅሞ እንዴት ነበር መልዕክቱን ያስተላልፍ የነበረው የሚለውን ለማሳወቅ
7. የትንቢት መንፈስ ማለት ምን ማለት ነው?
8. የትንቢት መንፈስ ጽሁፍ አላማው ምንድን ነው?
9. የኤሌን ጂ ዋይት የሕይወት ልምምድ ምን ነበር?
10. የኤሌን ጂ ዋይት አስተምህሮዎች ምንድን ናቸው?
11. ኤሌን ጂ ዋይት ስለአየቻቸው ራዕዮችና ህልሞች የተሰጡ ምስክርነቶች
12. መፅሀፍ ቅዱስ እና የትንቢት መንፈስ ጽሁፎች ያላቸው አንድነት
13. የትንቢት መንፈስ የተሰጠበት ዋና አላማ
14. የኤሌን ጂ ዋይት ስራዎች
15. የኤሌን ጂ ዋይት የሕይወት ታሪክ

1. የትንቢት መንፈስ ስጦታ አስፈላጊነት

አዳም እና ሔዋን ከተፈጠሩ በኋላ ሁለቱም በጣም ፍፁም እና በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠሩ ነበሩ፥ምድር እና መላውን እንዲገዙ ስልጣን ተሰጥቷቸውም ነበር፡፡ (ዘፍ 1፡ 26) አዳም መጋቢ እንደመሆኑ መጠን ከምንም ነገር በላይ የእግዚአብሔር ተጠሪ ነበር፤ መጋቢ ነው ስንል እግዚአብሔር የሰጠውን አደራ የሚወጣ ማለት ነው፤ የራሱ ያልሆነ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፋንታ ምድርን እንዲያስተዳድሩ ስልጣን ሰጥቷቸው ነበር፡፡

ምድርንም ብቻ እንዲቆጣጠር አልነበረም ስልጣኑ የተቸረው፣ ደግሞም የሰጠው ምድር መኖሪያውም እንድትሆን ነበር (ዘፍ 2፡8-15)። የእግዚአብሔር እቅድ አዳም እና ሔዋን ዘርን ተክተው ምድርን እንዲሞሏት፣ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ስለነበር ልጆቻቸውም የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባህሪ እንዲያንጸባርቁ ነበር፡፡ በተለይ ሔዋን ለባሏ መልካም እረዳት እንድትሆን ነበር የተፈጠረችው፣ ለእርሱም ፍጹም ገጣሚ ረዳት እንድትሆን አድርጓት ነበር የፈጠራት፣ በጣም ፍፁም የሆነች ሚስት፣ በጣም ፍፁም የሆነ ባል፣ በጣም ፍፁም የሆነ ቤት እና በጣም ፍፁም የሆነ አካባቢ እንዲኖራቸው አድርጎ ነው የፈጠራቸው፡፡ ይህ መለኮታዊ ዕቅዱ ለእነርሱና ከእነርሱም በኋላ ለሚመጣው ትውልድ በፈጠራቸው የታቀደ ዘላለማዊ ዕቅድ ነበር፡፡ መልካሙን ነገር ብቻ እንዲያውቁም እግዚአብሔር ይፈልግ ነበር፡፡

ሁሉን ነገር እንዲያደርጉም ተፈቅዶላቸው ነበር ነገር ግን መልካምና ክፉዉን ከምታስታውቅ ዛፍ እንዳይበሉ ተነግሯቸው ነበር (ዘፍ 2፡2-9)፤ ለዋንዶቹ አምላክ የተሰጠው ቀጥተኛ የሆነ ትዕዛዝም ፡፡ (ዘፍ 3፡3)፤ ዘፍጥረት 1፡31 ፍጥረት ሁሉ መልካም እንደ ነበር ይናገራል፡፡ መልካምና ክፉን የምታስታውቀው ዛፍ በራሷ መጥፎ አልነበረችም፡፡ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነጻ ሀሊና ተጠቅመው እርሱን እንደሚታዘዙ ለማወቅ ነበር ያስቀመጠው፤ ደግሞም ፍፁም ወደ ሆነው አምላክ እያደጉ እንዲሄዱ እና በእርሱ ላይ ሙሉ እምነት እንዲኖራቸውም ጭምር ለማስተማር ነበር፡፡ በአዳምና በሔዋን አዕምሮ ምንም አይነት ያለመታዘዝ ዝንባሌ አልነበረም፡፡ ፈተና በሰይጣን ቢመጣም እንኳን ለፈተና እጃቸውን ሳይሰጡ እንዲኖሩ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር (ራዕይ 12፡7-9)፤ የሰው ልጅ ባህሪው በጣም ፍፁምና ከመላዕክት ጥቂት ዝቅ ተደርጎ ነበር የተፈጠረው (መዝ 8፡5) አዳም እና ሔዋን በራሳቸው ፍላጎት በፈተና በመውደቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት አጎድሉ፡፡ ሰይጣን እባብን ተጠቅሞ ሔዋንን ከአሳሳታት በኋላ አዳም እያወቀ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላለፈ (ዘፍ 3፡6 እና 1ጢሞ 2፡4)።

‹‹ሴቲቱም ዛፉ ያማረ እንደሆነ ለአይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብ መልክ መልካም እንደሆነ አየች ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርሷም ጋር በላ›› (ዘፍ 3፡6) ልክ ጎጥያት ወዲያው ወደ ዓለም እንደገባ ውጤቱ በዓለም ላይ መታየት ጀመረ፡፡ አንዳንድ የታየው ለውጥ ሰው በተፈጠረበት ጊዜ የነበረው አይነት ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ አልቻለም፡፡ እግዚአብሔር እንደለመደው

ከሰዎች ጋር ለመገናኘት በመጣ ጊዜ አዳምና ሔዋን ተደበቁ፤ ኀጥያት እግዚአብሔርን እንደፈለገው ከሰው ልጅ ጋር እንዳይገናኝ ከለከለው ። መፅሀፍ ቅዱስ በእናንተና በእርሱ መካከል ኀጥያት ከለከላችሁ ይላል (ኢሳ 59፡2)። በኀጥያት ምክንያት በሰው አዕምሮ ውስጥ የመጡ ለውጦችን እንመልከት።

1. **የእግዚአብሔርን ፊት ማየት አልቻሉም**

ዘፍ 33፡20,20-23

2. **ክፉውን እና መጥፎውን ማወቅ ቻሉ**

ዘፍ 3፡22

የእግዚአብሔር ዕቅድ የሰው ልጅ መልካሙን ነገር ብቻ እንዲያውቅ ነበር የሚፈለገው ይህ ክፉውን የማወቃቸው ነገር በምርጫ እና በሰይጣን አማካኝነት መጥቷል ከመልካም ይልቅ የሰው ልጅ መጥፎውን ።

3.የሰው ልጅ ፈራ

ዘፍ 3፡8-10

አዳም እና ሔዋን ከዚህ በፊት ፍርሀት የሚባል አያቁም ነበር፤ የሚያስፈራቸው ምንም አልነበረም፤ ሙሉ ለሙሉ ከእግዚአብሔር ጋር ተቀናጅተው ይሰሩ ነበር። ፍጥረት ሁሉ ይታዘዛቸው ነበር፤ እግዚአብሔር በመካከላቸው በመገኘቱ ይደሰቱ ነበር፤ አሁን ግን ድምጹን ሲሰሙ ተሸሸጉ።

4. ለሞት የታዘዘ ሆነ፦

ዘፍ 2፡17

መክብብ 9፡5 / ዕብ 2፡15, 1ቆሮ 15፡26

5. የሰው ልጅ ራሱን መከላከል ጀመረ

ዘፍ 3፡2 በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው ለሰሩት ኀጥያት ኃላፊነት የሚወስዱት፤ ነገር ግን አዳም አንተ የሰጠሽኝ ሚስት እስከሚል ድረስ ተናገረ፣መተላለፉንና አመጹን በእግዚአብሔር ላይ አሳበበ።

3. **አዕምሮው (ለልቦናው) የተበላሸ ሆነ**

2ቆሮ 11፡3 በፊት የአዳም አዕምሮ ያልተበላሸ ስለነበረ፣ የውሎው ተዕዕኖ አልነበረበትም አሁን ግን በፊት እንዲሚያስበው አይደለም በኀጥያት ምክንያት የሚስበው አስተሳሰቡ እየተበላሸ ሄደ።

4. **የሰው ልጅ በስጋ አጉል ምኞት ተሞላ ሆነ**

ሮሜ 8፡6-7 ኀጥያት ከገባ ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት መተያየት አልቻለም። እነርሱን ለማስተማር በፊት እንደሚያደርገው ከፊለገ ለየት ያለ መንገድ መመስረት ነበረበት። በዘመናት የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዎችን ለመገናኘት፣ ፍቃዱን ለማሳወቅ እና ሰውን ከወደቀበት ኀጥያት ለመመለስ ሞክሯል።

<u>እነዚህ መንገዶች</u>

1. **መላእክት**

ዕብ 1፡14, መዝ 34፡7 መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው መልዕክት ያመጡ ነበር፡፡ ለምሳሌ

ዘሁልቅ 22:31-35፣

መሳፍንት 6፡11 ማቴ 1፡18-25

2. **ተፈጥሮ ስለ እግዚአብሔር ያወራል**

ሮሜ 1፡20 ዮሐንስ 14፡17 መዝ 19:12

ተፈጥሮ ቃል ሳያወጣ በዝምታ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ይመሰክራል፣ ይናገራል እንዲሁም ያወራሉ፡፡

3. **በኡሪም እና ቱሪም ይናገራል**

ዘሁልቅ 27፡21 በካህኑ ደረት ላይ በሚደረገው 12 ድንጋዮች እግዚአብሔር ይናገራቸው ነበር፡፡

4. **በህልም ይናገራቸው ነበር**

እግዚአብሔር በህልም ይገለፅ ነበር

ዘፍ፡37፡1

5. **ከሰማይ ድምፅ ይመጣ ነበር**

በጣም ጥቂት በሆኑ ቦታዎች ላይ ነው እግዚአብሔር በድምጽ ከሰማይ የተናገረው፡፡

ማቴ 3፡17 / ማቴ 17፡5

- ኢየሱስ ስምህን አክብረው ባለ ጊዜ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ነበር፣ ዮሐንስ፡ 12፡ 28
- በሲና ተራራ ላይ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምተው ነበር፡፡ ዘፀ፡19፡9-19
- እግዚአብሔር አንድ ጊዜ አሮንን እና ሙሴን በደመና ውስጥ ተናግሯቸው ነበር፡፡ ዘሁልቅ፡ 12፡5-6

6. **በመንፈስ ቅዱስ በግል ይናገር ነበር፡፡**

ምሳ፡ 3፡6 ኢሳ፡ 3፡21/ ማቴ፡ 10፡19-20

7. **በኢየሱስ በራሱ ይናገር ነበር፡፡**

በሰው ልጅ ህይወት ላይ በጣም ለውጥ የሚያመጣው ይህ የመገናኛ ዘዴ ነው፡፡

ዮሐ 14፡8-9 / ዕብ 1÷1-2

8. **በነብያት ይናገር ነበር፡፡**

አሞፅ 3፡7 "እግዚአብሔር አንዳች ነገር አያደርግም ለባሪያዎቹ ሳይናገር" መልዕክተኞችን ለእስራኤል ይልክ ነበር፡፡

ዘሁልቅ፡ 12፡6

ለምንድን ነው እግዚአብሔር ነብያትን የተጠቀመው?

የትንቢት ስጦታን በመጠቀም እግዚአብሔር የክርስቶስን የመጀመሪያ ምፅአት ለመናገር ችሎ ነበር፡፡ ዕብ 2፡17፣ የደህንነት እቅድን ለመፈፀም ክርስቶስ የግድ ሰው መሆን ነበረበት፣ በሰዎች መሐከል እንደ ሰው መኖር በሁሉ ነገር መፈተን በሰብአዊ ስጋ በመሆን ሙሉ በሙሉ ኀጥያትን ማሸነፍ ነበረበት፡፡ ኢየሱስ ወደምድር ከመምጣቱ በፊት በነብያት አማካኝነት ስለአመጣጡ በቅድሚያ እንዲታወቅ አድርጎ ነበረ ፡፡

1. ነብያት እግዚአብሔርን ወክለው በዚህች ምድር ይቆሙ ነበር፡፡ዘዳግም 18፡ 15 ፡፡
2. ነብያት ሁል ጊዜ ሰዎች ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋሉ ፡፡
3. በነብያት አማካኝነት ቀጥተኛ ግንኙነት ያደርጋል (ፊት ለፊት ሳይተያዩ) ፡ ፡
4. ነብያት በደህንነት እቅድ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ፡፡
5. ለሰዎች ለማስተላለፍ እንዲችሉ 1ቆሮ 10፡1 መልዕክቶቻቸውን በጥቅል መጽሐፍት ይጽፏቸው ነበር፣

ነብይ እና መልዕክቱ

ነብይ የሚለው ቃል ትርጉም ምንድ ነው?

ከዳዊት ከመጀመሪያዎች ቃል ውስጥ "የእግዚአብሔር መንፈስ በኔ ተናግሯል ቃሉ በአፌ ላይ ነው" 2ሳሙ· 23፡2 / 1ጴጥሮስ 1፡2 ፡፡

ነብያት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ሲናገሩ መልዕክቱ ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይቆጠራል፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስ ነብይ ማለት የእግዚአብሔር አፍ ማለት ነው በሌላ አገላለጽ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ማንኛውንም መልዕክት ለንጉስ/ ለሕዝብ ወይም በምድር ላይ ሊሚኖሩ ሁሉ መልዕክት የሚያስተላልፍ ማለት ነው ፡፡

በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ነብይ ተብሎ የተተረጎመው NABI ነው ፡፡ ለምሳሌ በዘፀአት 7፡1-2 እግዚአብሔር ሙሴ ለፈርኦን አምላክ አድርጌሀለው ይላል፡፡ ወንድምህ አሮን ነብይ ይሆናል ከዚያ ያዘዝሁህን ሁሉ ትናገራለህ ፤ ወንድምህ አሮን አፍ ይሆናል፡፡ ሙሴ በፈርኦን ፊት እግዚአብሔርን ወክሎ ይቆማል አሮን የሙሴ አፈቀላጤ ሆኖ ይሰራል፡፡

እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መልዕክቱን ያስተላልፋል ሙሴ ቃሉን ለፈርኦን ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር በእንዲህ ባለ ሁናቴ ሁልጊዜ ባይሰራም ነገር ግን የነብዩ ስራ መልዕክቱን ከእግዚአብሔር ወስዶ ለህዝቡ መናገር ነው፡፡ በዘዳግም 18 ላይ ‹‹ቃሌን በአፍ ላይ አደርጋለሁ ይላል ያዘዝኩህን ለህዝቤ እንድትናገር ›› ዘዳግም 18፡18 ‹‹ ነብዩ ›› የሚለው

ቃል በዚህ ቁጥር ላይ NABI ይላል፣ የእግዚአብሔርን መልዕክት የሚያስተላልፍ ሰው ማለት ነው ።

በኤርሚያስ ፡

በኤርሚያስ 1፡4-10

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ በእናቱ ሆድ ሳለ ለአህዛብ ነብይ አድርጎ እንደመረጠው፣ ኤርምያስ ግን ህፃን እንደሆነ መናገር እንደማይችል ተናገረ እግዚአብሔር ግን እንደሚልከው ያዘዘውን ሁሉ እንደሚናገር ነገረው እዚህ ላይ እንደምናየው ለነብያት እግዚአብሔር እራሱ ቃሉን በአፋቸው እንደሚያደርግ ነው፡፡

እግዚአብሔር ለነብዩ ኤርሚያስ እንዲህ ብሎት ነበር፣ ኤርሚያስር 15፡19 ላይ ‹‹ አንተ እንደ አፌ ትሆናለህ ›› በዘዳግም 18፡18 ላይ የሰጠውን ተስፋ ሲፈፀም እናያለን ። ነብይ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ የሚናገር ነው፡፡ አሞፅ 7፡15-16

አዲስ ኪዳንም በግሪክ ቃል ነብይ የሚለው ቃል ሲተረጎም Prophet / ነብይ / ማለት ነው፡ ፡ ትርጓሜውም ከእግዚአብሔር ተቀብሎ የሚናገር ማለት ነው ። Prophet / ነብይ / የሚለው በአዲስ ኪዳን አነጋገር ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን nabi ከሚለው፣ የነብያት አገላለፅ ጋር አንድ ነው፡፡ ሁለቱም ላይ እንደ እግዚአብሔር ሆኖ መናገር ማለት ነው፡፡ ማቴ 1፤22 / ዮሐዋ 3፡18 / ሐዋ 3፡21 አንብብ ።

እግዚአብሔር ነብያትን የመረጠው የኢየሱስ የደህንነት እቅድ ለመናገር ነው፡፡

ነብያት እና ሥራዎቻቸው

በጥንት ዘመን እግዚአብሔር መልዕክቱን ለማስተላለፍ የተለያዩ ሰዎችን በህልም ይገለፅላቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ነብያትን ለአገልግሎት ሲጠራ የእዕድሜ ገደብ አላስቀመጠም፡፡ መጥምቁ ዮሐንስን ከማሕጸን ለይቶታል፣ ኤርምያስን በልጅነቱ መርጦታል፣ ሙሴን በሰማንያ አመቱ ጠርቶታል፣ በጸታ ካልን ወንዶችንም ሴቶችንም ተጠቅሟል፣ በየዘመናቱ ለነብይነት አገልግሎት እግዚአብሔር እንደ ወደደ ብዙዎችን፣ ጠርቷል። እግዚአብሔር ሰዎችን ሲመርጥ እንደ ልቡ የሚጠቀምባቸውን ነበር። ለወደፊት ለአገልግሎት የሚያዘጋጀው ለስራ ገጣሚ የሆኑ ሰዎችን ነው ። 1ቆሮ 9፡19-22

እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ሰዎች
አብርሐም

አብርሐም ምንም አይነት *መፅሐፍ አልጻፈም* ፤ በጣም ቁልፍ የሆኑ ሚናዎችን በአዲስ ኪዳን እና በብሉይ ኪዳን ተጫውቷል። ጌታ ለአቤሜሌክ ሲናገረው አብርሀም ነብይ እንደነበር ተናግሯል። ዘፍ 20፡7 / ሮሜ 4፡13

ሳሙኤል

እንደ ሙሴ ቤተሰቦቹን ትቶ ወደ ጣኦት አምላኪዎች ነገስታት ከመሄድ ይልቅ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ካህኑ ኤሊ ነበር የሄደው በህፃንነቱ ። በእግዚአብሔር እና በሰው ፊት በሞገስ ያድግ ነበር፤ ሳሙኤል በጣም ስነ-ስርአት ባለው መንገድ በንፅኅና ያድግ ነበር፡1 ሳሙ12፡3 ። ሳሙኤል እንደ ነብይ ህዝቡን ፍርድ በመስጠት ያገለግል ነበር።

ዳዊት

1 ሳሙ 13፡14

ዳዊት ገና ታዳጊ ወጣት እያለ ገና በልጅነቱ ነበር በእግዚአብሔር ተመርጦ በነብዩ ሳሙኤል አማካኝነት የተቀባው፤ በጣም ጥቂት ሰዎች ነበሩ ዳዊት ከነበረው ችሎታ ላቅ ያለ እምነት ያሳዩት። ዳዊት በገናን ደርዳሪ፣ ገጣሚ፣ ዘማሪ፣ የጦር መሪም አዛዥ ፣ ህግ አውጭ ንጉስ ነበር። እነዚህ ነገሮች በጣም በትምህርት እና በልምድ የዳበሩ ነበሩ። የዳዊት መዝሙሮች የሚያሳዩት ዳዊት ከእግዚአብሔር የተሰጠው የመንፈሳዊ ስጦታዎች የበዙ እንደነበሩ ነው።

አሞጽ

አሞጽ በነብያት ትምህርት ቤት ገብቶ ያልተማረ ነው እድሉ እና አጋጣሚው ያልነበረው ሰው ነው፤ እግዚአብሔር ግን እሱን በማሰልጠን ለሥራው ገጣሚ ያደረገው ሰው ነው ።

አምዕ ፡ 1፡14 / 2፡3 /2፡9 / 3፡4 / 7፡10-17

እነዚህ ጥቅሶች ምን ያህል አስተሳሰቡ ትልቅ እንደ ነበር ያሳያሉ። ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መልዕክት በጥበብ ለማስተላለፍ ብቃት እንደ ነበረው ያሣያል።

ዳንኤል

ዳንኤል 1፡3-4 / 5፡29 / 6፡1-3 / 2፡47 / 6፡25-26 ምን አይነት ነብይ እንደነበር እነዚህ ጥቅሶች ይናገራሉ። ለማሳያነት የተሰጡትን ጥቅሶች ይመልከቱ።

ጳውሎስ

ከዕብራዊም ዕብራዊ የፈሪሳዊ ልጅ ብሎ እራሱን ለመግለፅ የተጠቀመበት መንገድ ነበር። በገማሊያ እግር ስር የተማረ፣ ክርስቲያኖችን ያሳደደ ቢሆንም እግዚአብሔር አሳዳጁን ለአህዛብ ሐዋሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ጠራው ሾመውም። የክርስቶስ ሰባኪ ሆነ ወንጌሉን ለማስተዋል ከመንፈስ ቅዱስ አዕምሮን ታደለ። የተማረ የሮም ዜግነት የነበረው ህይወቱን በመለወጡ ምክንያት በጋለ ፍላጎት አስቸጋሪ የነበረው ማንም ሰው ሊሰራ ያልቻለውን ሥራ በተሰጠው ጸጋ ልክ አከናውኗል።

ነብያት ክርስቶስን ለአህዛብ ያስተዋውቁ ነበር ።

ስለ እግዚአብሔር ይናገራሉ

1. የመጀመሪያው የነብያት አስፈላጊነት ነብያት እግዚአብሔርን በመወከል የሚናገሩ እንደሆነ አይተናል። የእግዚአብሔርን መልዕክት ለግል ፣ ለቤተሰብ ፣ ለአገር እና ለከተማ ወይም ለህዝብ ያስተላልፋሉ።

ከእግዚአብሔር ይህንን ኃላፊነት በመውሰድ አልግሎቱን በተቀበሉ ሰዎች አማካኝነት መልዕክት ለነብያቱ ያስተላልፋል።

2. ነብያቱም የተነገራቸውን ወይም የተገለጠላቸውን የእግዚአብሔርን አላማ ይገልፃሉ። አሞፅ 3፡7
3. በዚህ መሰረት የእግዚአብሔር ነብያት መሪዎችን በመምራት እና በመምከር ተግባራቸውን ያከናውኑ ነበር። (ኢሳ 36፡2 37፡6-7)

ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤት ለመስራት በልቡ ባሰበ ጊዜ ሃሳቡን ያጋራው ለነብዩ ለናታን ነበር፤ በዚህ መሰረት እግዚአብሔር ነብዩ ናታንን በመጠቀም ዳዊት ሳይሆን ልጁ ሰለሞን ቤተ መቅደስ እንደሚሰራለት ተናገረ። (2ኛ ሳሙ 7፡1 / 1ኛዜና 22፡14)

ዳዊት

በጣም በመጥፎ ወቅት በጥንት ጊዜ መሪዎች ከነብያት ምክርን ያገኙ ነበር።
ከስላሴ አንዱ የሆነው መልዕክቱን ለሰብአዊ ሰው ሲያስተላልፍ እናያለን ንጥያት ከገባበት ጊዜ አንስቶ ወደ ሰማይ ማንኛውንም ነገር በኢየሱስ በኩል ብቻ ነው ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የሚደረስው። ዳንኤል 8፡16 / ዳንኤል 9፡21 ወይም ሉቃ 1፡19-26
ከነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው መልአኩ ገብርኤል እንዴት አድርጎ መልዕክት ለነብዩ ለዳንኤል ሲያመጣ እንደነበረ እናያለን ።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ እንዴት አድርጎ መንፈስ ቅዱስ በነብያት ላይ እንደሚመጣ ለማየት እንሞክራለን።

1 ሳሙኤል 10፡10 / 2ኛ ዜና ካልዕ 15፡1-2 / ሕዝ 2፡12 / ህዝ 3፡12-14 / ህዝ 8፡3 ሕዝ 11፡5 / ሕዝ 37፡1 / እዩኤል 2፡28 / ራይ 1፡8 ይህ የሚያመለክተው መለኮታዊ መልዕክት ነብያት ሲቀበሉ መንፈስ ቅዱስ እንደሚቆጣጠራቸው የሚያሳይ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በነብያት ላይ በሚሆን ጊዜ የሚከሰተው።

የዳንኤል ልምድ፣

ዳንኤል 10፡8-9 /10፡4 ፣ ዘሁልቅ 12፡6።

1. ለዳንኤል ልዩ የሆነ ነገር ተገልጦለት ነበር።
2. ነብዩ ሐይሉን (አቅሙን) አጥቶ እና መሬት ላይ ወድቆም ነበር።
3. ምንም እንኳን ጥልቅ እንቅልፍ ላይ ቢሆንም የመልዓኩን ድምጽ ይሰማ ነበር።
4. በመጀመሪያ ኮልታፋ የማይናገር ነበር ፣ነገር ግን የሰው ልጅ የሚመስለው ከንፈሩን በዳሰሰው ጊዜ መናገር ጀመረ።
5. አይተነፍስም ነበር።
6. ጥንካሬም ተሰጥቶት ነበር። ነብያት ራዕይንና ሕልምን በሚቀበሉበት (በሚያዩበት) ጊዜ የሚታዩ ባህሪያት መካከል ይገኙበታል።

<u>በህልም እና በራዕይ፤</u>

በዘሁልቅ 12፡6 እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ በህልም እና በራዕይ እንደሚናገር ይናገራል፡ ፡ በዳንኤል 7 እና በዳንኤል 8 ላይ 1-2-15-17 ነብዩ ዳንኤል ራዕይ እንዳየ ይናገራል። የመለኮት ፍቃድ ለነብዩ የሚታየው ወይም የተገለጠለት በህልም እና በራዕይ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ፈቃዱን(እቅዱን) በምድርም ላይ በሰው የግል ሕይወት የሆነውንና ሊሆን ያለው በህልምም ሆነ በራዕይ ለነብያቱ ይገልጥ ነበር ።

ዳንኤልን ስንመለከት ጥልቅ እንቅልፍ ተኝቶ እንደነበረ ይናገራል ህልሙን ሲያይ ግን ይሰማ ነበር። በአካባቢው ያለውን ነገር ምንም አያውቅም ነበር ነገር ግን በህልሙ እግዚአብሔር የሚያሳየው እና የሚለውን ነገር ሁሉ ያስተውል ነበር። መንፈስ ቅዱስ በነብዩ ላይ በሚሆንበት ጊዜ ራዕይውን እንዲቀበል ያዘጋጀዋል ሐሳቡንም ሙሉ በሙሉ ከነባራዊው ዓለም ጋር እንዲስማማ አድርጎ ለዳንኤል ይገልጥለት ነበር፤ ዳንኤል ምዕራፍ 9 እና 10 / 11፡24 ይመልከቱ።

ይህ ማለት እንደ ፀሐፊው ሀሳብ ሰማያዊውን ነገር እኛ በምናስተውለውና ምድር ላይ ለሚኖር ሰው ሁሉ ሊረዳው በሚችለው ሁኔታ ያስቀምጠዋል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ራዕይዋችና ሕልምች ጊዜአቸውን ጠብቀው የሚስተዋሉ ሲሆኑ ደግሞም ለሚያየው ነብይ እንኳን ትርጉማቸው ዝግ ሊሆን (ላያስተዋለው) ይችላል፡፡

ነብያት እንዴት አድርገው ነበር ለህዝቡ መልዕክቶቻቸውን የሚያስተላልፉት?

እግዚአብሔር የተለያዩ ሰዎችን ነብያት እንዲሆኑ ያስነሳል ፡፡ የተለያዩ መልዕክቶችን በነብያት አማካኝነት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቅም መልዕክቱን ሲያስተላልፍ ነበር፡፡ የሁሉም ነብያት መልዕክቶች በጽሁፍ የቀረበ አልነበረም፣ ብዙ መልዕክቶች እንደ ስብከት እና በውይይት መልክ የቀረቡ ነበሩ ፡፡ ነገር ግን በመፅሐፍ መልክ ከተፃፈልን በኋላ ለቤተክርስቲያናት እና ለነገስታት የተመሰከረበት መንገድ ነበር፡፡ የእያንዳንዱን ነብይ መልዕክት እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በመጠበቅ ለእኛ በመጽሐፍ ቅዱስ መልክ እንዲደርስ አድርጓል፡፡

እግዚአብሔር የእርሱን መልዕክት ለህዝቡ ወይም ለአገልጋዮቹ የሚያስተላልፍበት ሦስት መንገዶች ፡፡

1. Oral
2. Written form
3. Enacted

Oral ቃል በቃል (በአንደበት)

ከስላሴ አንዱ የሆነው እግዚአብሔር ወልድ በሰውና በእግዚአብሔር አብ መሃል መካከለኛ በመሆን መልክቱን ለሰብአዊ ሰው ሲያስተላልፍ እናያለን፡፡ ጎጥያት ከገባበት ጊዜ አንስቶ ወደ ሰማይ የሚደረግ ማንኛውም ነገር የሚከናወነው በኢየሱስ በኩል ነው፡፡ ገብርኤል ከእግዚአብሔር የተላከውን መልዕክት እንዴት አድርጎ ለዳንኤል ይሰጠው የነበረው?

ነብይ እና መልዕክቱ

ከዳዊት የመጨረሻ ቃላት መሀከል ‹‹ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ ቃሉቹም በአፌ ውስጥ ነበር›› 2ሳሙኤል 23፡2፡፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ከተናገሩት ውስጥ ጴጥሮስ 2ጴጥሮስ 1፡21፡፡ ነብያት በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገሩ መልዕክታቸው ልክ እንደ እግዚአብሄር ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሙሴ በፈርኦን ፊት እንደ አምላክ ሆኖ ቆሞ ነበር፣ እግዚአብሔር ፍቃዱን በሙሴ በኩል ይገልፅ ነበር፡፡ ሙሴ ቃሉን ለአሮን ያስተላለፍ ነበር አሮን መልዕክቱን ለፈርኦን ይናገር ነበር፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ

የሚሰራ ባይሆንም ሁልጊዜ ከላይ ከሰማይ የሚሰጠውን መልዕክት የሚያስተላልፍበት አንዱ መንገድ ነው። በብሉይ ኪዳን ነብይ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ (ናቢ) ማለት ሲሆን የእግዚአብሔርን መልዕክት የሚናገር ማለት ነው። መዕሐፍ ቅዱስ እንደሚለው " ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል" ዘዳግም 18፥18። እግዚአብሔር በነብዩ ኤርሚያስ በኩል የተደረገውን ንግግር እስቲ እንይ፣ ነብዩ ኤርሚያስን በመጀመሪያ በእናቱ ሆድ እያለ እንደመረጠው እግዚአብሔር ተናግሯል ኤርሚያስ 1፡5 ። ኤርሚያስ ግን በቁጥር 6 ላይ እሱ ልጅ እንደሆነና መናገር እንደማይችል ምላሽ ለእግዚአብሔር ሰጠ ። እግዚአብሔር ለኤርሚያስ ሲነግረው ወዲያው ኤርሚያስ ሲመልስ መልዕክቱን ለመናገር እንደማይችል ተሰምቶ ነበር። ኤርሚያስ 1፡7-9 /15፡49 ፡ በዘዳግም 18፡18 ላይ ቃሉን በነብያት አፍ ላይ እንደሚያስቀምጥ ነበር የተናገረው ። ስለዚህ መልዕክተኛው ያለ ፍርሀት ምንም አይነት ውጤት እንኳን ቢያስከትልም መልዕክቱን የሚያስተላልፍና የሚናገር መሆን አለበት።

እግዚአብሔር እንዴት ነው ነብያትን የሚያናግራቸው።

በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ እግዚአብሔር ለህዝቡ መልዕክት በሚስተላልፍበት ወቅት አንድ ወጥ ዘዴ ብቻ እንደሚጠቀም የሚያሳይ ነው ። በተለያየ መንገድ መልዕክቱን ለማድረስ ተጠቅሟል። አንዱን ሂደት እንመልከት በዮሐንስ ራዕይ ላይ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ፤ ኢየሱስ ደግሞ ለመልአኩ ፣ መልአኩ ደግሞ ለዮሐንስ፤ ዮሐንስ ደግሞ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መልዕክቱን እንደሰጠ ይናገራል። ዮሐንስ ራዕይ 1፡1-4

አዲስ ኪዳንን ስንመለከት በብዛት መልዕክቶቹ በደብዳቤ መልክ ነበር የተዘጋጁት አስራ አራቱ የጳውሎስ ጽሁፎች በደብዳቤ መልክ ነበሩ የተፃፉት ። ቆላ 4፡16 / 2ጴጥሮስ 5፡12 ለተጨማሪ ጥቅስ ኤር 29፡2 / ዜና ካልዕ 21፡12-15

Enacted Communication

በመፅሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራ ላይ በብሉይ ኪዳን ዘመንም ይሁን በአዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ህዝቦቹን በምሳሌ ይናገር ነበር። ነቢያት ለህዝቡ በምሳሌ ያልተናገሩበት ጊዜ ነበር፣ ነገር ግን ብዙዎቹ ደግሞ በምሳሌ ተናግረው ነበር።

1 ሳሙኤል 15፡1-35 / ኤርሚያስ 10፡1-6 1ሳሙኤል 15-28። የሳኦል ልብስ መቀደዱን ድርጊት በመጠቀም መንግስቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ላይ እንደወሰደበት ነገረው።

ነብያቱ የተቀበሏቸው መልዕክቶች በአራት ይከፈላሉ።

1. አንዳንድ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እራሳቸው በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው መልዕክቱን በተቀበሉት አገልጋዮች ስም የሚታወቁና የተሰየሙ ሆነው እንናገኛቸዋለን፡፡ ለምሳሌ ፦ እንደ የሕግ መጽሐፍት (የሙሴ መጽሐፍት)፣ ኢሳያስ፣ ኤርሚያስ የመሳሰሉት ናቸው፡፡
2. መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም አይነት ነገር ያልፃፉ ነብያት አሉ፣ ነገር ግን ትምህርታቸው እና የሕይወት ታሪካቸው በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፃፉ አሉ፡፡ ለምሳሌ ኤልያስ / ኤልሳዕ / ሄኖክ የመሳሰሉት፡፡

3. ነቢያት ሆነው አጠቃላይ ምስክርነት የሰጡ አሉ፡፡ ለእነዚህ ነቢያት ምንም አይነት በመፅሐፍ ቅዱስ ስፍራ ያልተሰጣቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሰባዎቹ ሽማግሌዎች (በሙሴ ጊዜ የነበሩ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ) ትንቢት የተናገሩ ናቸው፡፡ 1ኛ ሳሙ 10፡5 -10 / 2ሳሙ 19፡18-24፡፡ ሌሎች ነቢያት ደግሞ መልዕክት የፃፉ ግን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስማቸው ያልተጠቀሰ ናቸው ለምሳሌ እያሱ 10፡13 / 2 ሳሙኤል 1፡18 / 2 ዜና መዋል 12፡15 / 7፡29 የእነዚህ ነቢያት መልዕክት በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚያ ጊዜ ብቻ የሚያገለግል መልዕክትን የያዘ ስለነበር ነው፡፡

የእነዚህ ነብያት መልዕክቶች መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልገቡበት ምክንያት እግዚአብሄር አስፈላጊ ያልሆነ መልዕክት ስለሰጣቸው አይደለም ነገር ግን ለወደፊቱ ትውልድ ምንም አይነት መልዕክት የሚያስተላልፉት ነገር ሰለሌላቸው ነው፡፡ ለጊዜው የሚሆነውን መልእክት አስተላልፈው አብቅተዋል ። እነዚህ መልክቶች ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር አይጋጩም 2ኛ ጴጥሮስ 1፡21 ።

እነዚህ ጽሑፎች ከመፅሐፍ ቅዱስ ጎን አብረን የምናያቸውን አይደሉም (cannon) በዚህ ጊዜ የሚያስፈልገውን መልዕክት አስተላልፈው ያበቁ ናቸው፡፡ በዚያው በአንዱ መንፈስ ሰዎች ተመርተው የፃፏቸው ናቸው ። እነዚህ ጽሁፎች ሰዎችን ወደ እምነት እና እግዚአብሔርን ወደ ማመን የሚገፋፉ ናቸው፡፡

ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ሁልጊዜ የሃሰትን ነገር ያደርጋል ። ብዙዎችን እግዚአብሔር ለበረከት ያደርጋቸዋል፣ ሰይጣን ለጥፋት ያመጣውን እግዚአብሔር ለበጎ ነገር ይቀይረዋል ።

ብዙዎቹ በአታላዩ ሰይጣን የተፈጠረውን የእሁድ ሰንበት ከእውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ሰባተኛውን ቀን የቅዳሜ ሰንበትን ትተው በእሁድ ቀን ያመልካሉ፡፡ በመንፈስ እና በእውነት አምልኩ የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል በልማዳዊ አምልኮ ለውጠውት እናያለን፡፡ ሌላው እንኳን ቢቀር ለጤንነታችን ተስማሚ የሚሆነውን አትክልት እና ፍራፍሬ መርዛማ በሆኑ ምግቦች ተክተዋቸው እናያለን ። እንዲሁም ደግሞ የሰይጣንን የማታለያ ትምህርቶቹን በነብያቱ በኩል እግዚአብሔርን ሊያስወግድ እቅድ አለው በተለይ በሐሰተኛ ነብያትቶች ትምህርቶችን በመስጠት ወይም ሐሰተኛ ነብያትን በማስነሳት ማቴ፡24÷1-40 ።

የሐሰተኛ ነብያት ስራ

1. የሰዎችን ልብና አዕምሮ ከእግዚአብሔር መልዕክት ማራቅ እና ስህተትን እንዲቀበሉ ማድረግ፡፡
2. በተሳሳተ መንገድ እግዚአብሔርን እንዲያስተውሉ በማድረግ የሐሰትን ነገር በመጠቀም እውነትን ሰዎች እንዳያዩ ማድረግ፡፡

ከመዕሐፍ ቅዱስ አንጻር አንዳንድ የነብያት መለኪያዎች፡፡

የነብዩ መልዕክት ከእግዚአብሔር ወይም ከሰይጣን የተቀበው መሆኑን የምንለይባቸውን መንገዶች መዕሐፍ ቅዱስ አስቀምጧል፡፡ የነብያቱ ትምህርቶች በእርግጠኝነት ከየት እንዳመጣ በመልዕክቶቹ መለየት እንችላለን፡፡ መዕሐፍ ቅዱስ ውስጥ አራት የነብያት መለኪያዎች ተቀምጠዋል፡፡

እነዚህ አራት የነብያት መለኪያዎች ማንኛውንም ነብይ ላይ ልንመዝንባቸው እንችላለን፤ ነብይ ነኝ ብሎ እራሱን የሚጠራን ሁሉ እንድንለካበት መዕሐፍ ቅዱስ አስቀምጦታል፡፡ ከእነዚህ ከዋና መለኪያዎች በተጨማሪ ሌሎች የነብያት መፈተኛዎችን ማካተት እንችላለን፡ :

1. የመጀመሪያው ነብያትን የምንለካበት መመዘኛ

ኢሳ 8:20

ወደ ‹‹ ሕግ ›› እና ‹‹ምስክር›› በሚለው አነጋገር ላይ ጥያቄዎች ይነሳሉ ፣ ነገር ግን በግልፅ ይህ ማለት መለኮታዊ የመዕሐፍ ቅዱስ ቃልን በመጠቀም በነብያት የተነገረውን የመመርመር አስፈላጊነትን ያሳያል፡፡ ማንኛውም ነብይ መዕሐፍ ቅዱስ ካስቀመጠው መመሪያ የተለየ እይታን የሚናገርና የሚያስተምር ከሆነ ይህ ነብይ ሀሰተኛ ነብይ ነው፡፡ የስህተት ትምህርት አንድ እንኳን ቢሆን ከእግዚአብሔር የተላከ አይደለም፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር የተላኩ (የተነሱ) ነብያት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው እንደተናገሩ ሁሉ ነብይ ነኝ የሚሉ ሁሉ የሚተነብዩት ወይም የሚናገሩት ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚቃረን ነገር ሊኖረው አይገባም፡፡

ለምሳሌ፦ ነብያት እንዴት እንደሚስማሙ አንዱ ከአንዱ ከፃፈው ጋር ጥቂት ማሳያዎችን እንመልከት

እዮብ 14፡12 / ሕዝቅኤል 18 ÷20 (እዩብ ከሀዝቅኤል ጋር ይስማማል)

መዝ 115÷ 17 / ዮሐንስ 11 ÷ 14 (ዳዊት ከዮሐንስ ጋር ይስማማል)

መክብብ 9÷ 5 / 1 ተሰሎንቄ 4÷13 (ሰለሞን ከጳውሎስ ጋር ይስማማል)

ኢየሱስ እና የወንጌል ፀሐፊዎች፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉ ነብያቶች የክርስቶስ መወለድን በትክክል ተንብየዋል

ለምሳሌ፦ በማቴዎስ ወንጌል የተፈጸሙ ቀደም ብለው የተተነበዩ የነብያት ትንቢቶች

ማቴ 1፡23 →	ኢሳ 7፡14	ማቴ 8፡17 →	ኢሳ 53፡4 →
ማቴ 2፡6 →	ሚኪያስ 5፡12	ማቴ 11፡10 →	ሚልኪያስ 3፡1 →
ማቴ 2፡17 →	ኤር 31፡15	ማቴ 12፡18 →	ኢሳ 42፡1 →
ማቴ 3፡3 →	ኢሳ 40፡3	ማቴ 13፡14 →	ኢሳ 6፡4 →
ማቴ 4፡14 →	ኢሳ 9፡1-2	ማቴ 21፡16 →	መዝ 8፡2

1.1 ማንኛውም የትንቢት መንፈስ አለኝ ብሎ የሚመጣ ሁሉ እነዚህን መፈተኛዎች ማማላት አለበት፡፡
1.2 መፅሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን የነብያት መፈተኛዎች ማለፍ አለበት፡፡
1.3 በጣም ጥሩ የሆነና የሚያስገርም የነብያትን መንፈስ መመዘኛ በኤርሚያስ 28 ላይ እናገኛለን፡፡

መፈተኛ ሁለት

"በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" ማቴ 7፡20

ይህንን ማስጠንቀቂያ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በተራራው ስብከት ላይ ነበር የተናገረው ከሐሰተኛ ነብያት ተጠንቀቁ ይላል፡፡ ደግሞም በቁጥር 15 ላይ መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ ያፈራል በማለት ይደመድማል፡፡

"የተበላሸ ዛፍ መጥፎ ፍሬ ያፈራል" ይላል፡፡ ኢየሱስ እራሱ ሌሎች ነብያትን የምንፈትንበትን መንገድ አስቀምጧል ነብያቱ በህይወታቸው ምን አይነት ፍሬ አፍርተዋል? ትምህርታቸው ምን ያህል ተፅዕኖ በሌሎች ላይ አሳድሯል? በቤተክርስቲያን ምን አይነት ተጽዕኖ ያለው የሕይወት ዘር ዘርተዋል? ብለን ማየት አለብን፡፡

የነብያቱ ሕይወት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔርን ፍጹም ባህሪ የሚያሳይ መሆን አለበት፣ እግዚአብሔር ራሱ በሚያስቀምጠው ቅደመ ሁኔታ ምክንያት አንዳንድ ትንቢቶች በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ በተናገሩለት ዘመን ያልተፈፀሙ ትንቢቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ነብያቶቹ የተናገሩት በታሪክ ውስጥ ተፈፅሞ እናየዋለን ወይም የሚፈጸሙበትን ዘመን ገና የሚጠብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ስለሚመጣው መሲህ አስቀድመው ተናግረው የነበረ የእነዚህ ትንቢቶች ፍጻሜ በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ ተከናውኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህም ቀድሞ ተነግሮ የነበረውን ትንቢት ትክክለኛነቱን እናረጋግጣለን፡፡ ነብዩ ዳንኤል የመንግስታትንና የሕዝቦችን ታሪክ ከባቢሎን ዘመን ጀምሮ፣የእኛንም ዘመን አካቶ እስከ ዘመን ፍጻሜ ድረስ በተገለጠለት ትንቢት አማካኝነት በሚገባ መልዕክት አስቀምጦት እናገኛለን፡፡ እግዚአብሔር ገና ሊመጣ ያለውን ነገር ሁሉ ከመሆኑ በፊት አስቀድሞ እንደሚያውቅ ይህ ትንቢት ማሳያ ነው፡፡

ሌሎች የትንቢት አፈታቶች (principle of condition prophecy)

በቅድመ ሁኔታ የሚነገሩ ትንቢቶች
ምሳሌ ፡- ኤር 18፡7-10

እንደዚህ ያሉ የትንቢት አይነቶች ሲያጋጥሙን በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ትንቢቶችን መመልከት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህን አይነት ትንቢት ሊያስረዳልን የሚችለው በትንቢተ ዮናስ መጽሐፍ ውስጥ እናገኛለን፡፡

ዮናስ በአርባ ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች ብሎ ለዛች ከተማ ሕዝብ ተናግሮ ነበር፡፡ የተናገረው ትንቢት ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ (condition) አላስቀመጠም ነበር ዮናስ 3፡4፡፡ ምንም አይነት የማምለጫ መንገድ አልቀረበም፡፡

“ዮናስም የአንድ ቀን መንገድ ያህል ወደ ከተማይቱ ውስጥ ሊገባ ጀመረ ጮኾም በአርባ ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች አለ፡፡” ዮናስ 3 ቁ 4

ነገር ግን ንጉሱ እና ህዝቡ ንስሀ በመግባታቸው ምክንያት ከተማዋ አልጠፋችም፡፡ በዚህ ምክንያት ዮናስ በጣም ተቆጣ ምክንያቱም ሐሰተኛ ነብይ እንዳይባል ስለፈራ፡፡

ወሬውም ወደ ነነዌ ንጉሥ ደረሰ፤ እርሱም ከዙፋኑ ተነሥቶ መጐናጸፊያውን አወለቀ ማቅም ለበሰ፥ በአመድም ላይ ተቀመጠ፡፡

አዋጅም አስነገረ፤ በነነዌም ውስጥ የንጉሡንና የመኳንንቱን ትእዛዝ አሳወጀ፤ እንዲህም አለ፦ "ሰዎችና እንስሶች ላሞችና በጎች አንዳችን አይቅመሱ፤ አይሰማሩም ውኃንም አይጠጡ፤

ሰዎችና እንስሶችም በማቅ ይከደኑ ወደ እግዚአብሔርም በብርቱ ይጩኹ፤ ሰዎችም ሁሉ ከክፉ መንገዳቸውና በእጃቸው ካለው ግፍ ይመለሱ።"

እኛ እንዳንጠፋ እግዚአብሔር ተመልሶ ይጸጸት እንደ ሆነ፥ ከጽኑ ቍጣውም ይመለስ እንደ ሆነ ማን ያውቃል?

የነነዌ ንጉስ ከእግዚአብሔር የተላከውን የፍርድ ትንቢት በመስማት፣ በመቀበልና በማመን የንስሐ የጾም ጸሎት በከተማዋ አወጀ በዚህ የእግዚአብሔርን ምህረት ተማጸነ፤ እግዚአብሔር የነነዌን ንጢአት ይቅር አለ። ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ስንመለከት የተነገረው የትንቢት አይነት ቅድመ ሁኔታዊ ነበር፤ ስለዚህ ነብዩ ዮናስን የትንቢቱ አለመፈጸም ሐሰተኛ ነብይ ሊያሰብለው አይችልም ማለት ነው። ካነሳነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደምንረዳው የተነገሩት ትንቢቶች እግዚአብሔራዊ በሆኑ ትክክለኛ ምክንያቶች ትንቢቶቹ እንደተነገረው ላይፈጸሙ ይችላሉ።

ነብያት የተናገሩት ሳይፈፀም ሲቀር ሐሰተኛ ነብያት የሚባሉት ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረንና ፍጻሜን ያላገኘ ሲሆን ነው።

እነዚህን ነገሮች እንዴት አድርገን እንደምንለይ እግዚአብሔር መመሪያውን (Decision and Attitudes) ሰጥቶናል።

በኤርሚያስ 18 ላይ እንደምናነበው ሁሉም የእግዚአብሔር በረከቶች ወይም ቅጣቶች በሁኔታዎች (condition) ላይ የተመሰረቱ ናቸው። የተቀመጠው መመሪያ (condition) ቢኖረውም ባይኖረውም የትንቢቱ አፈፃፀም ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው እምነት ላይ የተመሰረተ ነው ።

የትንቢት መንፈስ ምን ማለት ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ በሰይጣን እና በክርስቶስ መካከል በሰማይ ጦርነት እንደተካሔደ ይናገራል፡ ፡ ጠላት ዲያቢሎስ እንደተሸነፈ አንድ ሦስተኛውን መላእክት ይዞ ወደ ምድር እንደተጣለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በራዕይ ዮሐንስ 12፡6-8

‹‹በሰማይ ታላቅ ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻለም ከዚያም ወዲህ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም›› ሰይጣን ብቻ ሳይሆን መላእክቱም አብረው ወደዚህ ምድር ተጣሉ። ዘንዶው ወደ ምድር እንደተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደደ›› (ቤተ ክርስቲያን) በራዕይ ዮሐንስ 12፡1-8

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን ለዘመን ለዘመናት ለዘመን እኩሌታ እንደተሳደደች በብዙ ቦታ ይናገራል። ለምሳሌ ዳንኤል 7 ፣ ራዕይ 12 እና 13 ስናነብ ቤተክርስቲያን በሰይጣን እና በወኪሎቹ ብዙ ችግር ደርሶባት ነበር።

ዘመን = 1 ዓመት ማለት ነው።

ዘመናት = 2 ዓመት ማለት ነው።

የዘመን እኩሌታ = 6 ወር ማለት ነው

አጠቃላይ 3 ዓመት ተኩል = 42 ወር= ማለት ነው

በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ 1260 ዓመታት ስደት ደርሶባቸው ነበር በታሪክ እንደምንረዳው ይህ ዘመን የጨለማ ዘመን በመባል ይታወቃል።

ከዚያም በመቀጠል ሰይጣን በፊት ያደረገው ስደት ሳይበቃው ከዘሯ (ከቤተክርስቲያን) ጋር ውጊያ እንደቀጠለ ይናገራል። ዮሐንስ ራእይ 12፡17 "ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጠብቁትን እና የኢየሱስ ምስክር ያላቸውን ከዘሯ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ በባህር አሸዋ ላይ ቆመ።" ራዕይ 12፡17 እንደሚናገረው የሰይጣን ትልቁ ጥላቻ ወይም በመጨረሻ ዘመን ላይ የሚዋጋው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጠብቁትንና የኢየሱስ ምስክር ያላቸውን እንደሆነ ይናገራል። የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሲል 10ቱን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ማለት ነው። እና ሁሉንም የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ያጠቃልላል ማለት ነው። ደግሞ የኢየሱስ ምስክር ሲል በራዕይ ዮሐንስ 19፡10 ላይ ሲፈታው የትንቢት መንፈስ_እንደሆነም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል።

ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ የትንቢት መንፈስ ስጦታ ነው 1ኛ ቆሮ 12፡10 እና ኤፌሶን 4፡11 ትንቢት እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን እንድትመራበት የሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ነው። እግዚአብሔር እስከ ዘመን መጨረሻ ድረስ ነብያትን ለመላክና በተለይም ለቅሬታዎቹ የትንቢት መንፈስን ለመስጠት ተስፋ ሰጥቶ ነበር።

አሞጽ 3፡7 / ኤፌ 4፡11-13 / ዩሐንስ 16፡7-14 / ኤዮኤል 2፡28 / ራዕይ 12፡17 እና 19፡ 10

ይህ የትንቢት መንፈስ ስጦታ በመጨረሻ ዘመን የምትኖር ቤተክርስቲያን መለያ ነው። የ7ኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የኤለን ጂዋይት ጽሁፎች ለቤተክርስቲያን ተግሳጽ እውነተኛ መልእክቶች መሆኑን ታምናለች ፣የትንቢት መንፈስ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የማንኛውም ትምህርት እና ልምምድ መፈተኛ መሆን እንዳለበት በግልፅ ይናገራል።

በመጨረሻው ዘመን ሐሰተኛ ነብያቶች የተመረጡትን እንኳን እንደሚያስቱ ማወቅ እንዳለብን ተነግሯል። ማቴዎስ 24፡11-24 እንዲሁም በመጨረሻ ዘመን በቅዱስ ቃሉ እውነተኛው መንፈስ ቅዱስ በሃይል እንደሚሰራ ተነግሮናል።

ባለ ራእዩ ዮሐንስ በመጨረሻ ዘመን ቅሬታ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ህግ የምትጠበቅ የኢየሱስ ምስክር ያላት ናት ይላል (keep the commandment of God has the testimony of Jesus Christ) ዮሐንስ **12:17**

የሐዋሪያው ጳውሎስ

የሐዋሪያው ጳውሎስ የኢየሱስ ምስክር (testimony of God) እያለ በተለያዩ ቦታ ጠቅሷል

2ኛ ጢሞ 1፡8 ።

የሰባተኛው ቀን ኢንድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የእግዚሐብሔር ትዕዛዝ ወይም የኢየሱስ ምስክር የሚለውን የምታስተውለው በመጨረሻ ዘመን የሚኖሩ የእግዚብሔር ህዝቦች የእግዚአብሔርን ህግ በሙሉ የሚጠብቁ (10ቱን ትዕዛዛት) የሰባተኛውን ሰንበት ቀን ጨምሮ ማለት ነው። የኢየሱስ ምስክር የሚለው ደግሞ እውነተኛ እና ዘለአለማዊ ወንጌል በእውነተኛ ነብያት የተሰጠው መሆኑን የሚያምኑ (*የኤለን ጂ ዋይት* Ellen G white) ፅሁፍን ጨምሮ ማለት ነው።

የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተ-ክርስቲያን አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ትንቢትን መናገር እንደሆነ ታምናለች (one of the gift of the holy sprite is spirit of prophecy) ይህ የትንቢት ስጦታ አንዱ የቅሬታዋ ቤተክርስቲያን መለኪያ ነው። ይህም የተገለጸው በኤለን ጂ ዋይት አገልግሎት አማካኝነት ነው። **E.G. white our foundational belief #17**

የኢየሱስ ምስክር ወይም የትንቢት መንፈስ የሚለውን ከኤለንጂ ዋይት (E.G. white) ጋር በተያያዘ ብቻ ሊዉል አይገባም። የእግዚአብሔር ባሪያዎች የተናገሩት በሙሉ የእግዚአብሔር ትክክለኛ መልዕክት ነው።

ለምሳሌ ፦ ለመመሪያ (instruction) የተሰጡ ፣ ለማበረታቻ የተሰጡ ፣ እንዲሁም ለተግሳጽ የተሰጡት በእግዚአብሔር በተመረጡ ነብያት ነው። በራእዩ ዮሐንስ 1:29/ 6:9 / 12:17 በመጨረሻ ዘመን ለምትኖረው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን መለያዋ የትንቢት መንፈስ ስጦታ ነው በኤለንጂ ዋይት እንደተሰጠው (EllenG. white) ማለት ነው።

የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በሙሉ ልቧ እነዚህ የኤለን ጂ ዋይትን ጽሁፎች ከእግዚአብሔር የተነገሩ (የተሰጡ) በመጨረሻ ዘመን ለሚኖሩ ህዝቦች እንደሆነ ታምናለች፡ :

መሰረታዊ እምነቶች በሚለው መጽሀፍ ላይ ገጽ 17 "እንደ እግዚአብሔር መልዕክተኛ የኤለን ጂ ዋይት ፅሁፎች ህጋዊ የሆኑ መሰረታዊ ጽሁፎች ሲሆኑ ለቤተክርስቲያን መፅናናትን፣ ምክርን እና የማረሚያ ነገሮችን ይሏል" ይላል። ለሁሉም አይነት ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እውነተኛ መለኪያ እንደሆነ የትንቢት መንፈስ ፅሁፎች በግልጽ ይናገራሉ።

እዩኤል 2፡28፡ / የሐዋ2፡14-21 / ሕዝ 1፡1-3 / ራይ12፡17 /ራይ19፡10

ሁሉም የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች በትንቢት መንፈስ ማመን አለባቸው? ሌሎችም ክርስቲያኖች ጨምሮ **አዎን** ይገባል!።

መጽሀፍ ቅዱስ ይናገራል ሁሉም ሰው በትንቢት መንፈስ ማመን እንዳለበት 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡20-21 ‹‹ "መንፈስን ሁሉ አትናቁ ሁሉን ነገር ፈትኑ መልካም የሆነውን ነገር ያዙ" ይላል

1 ቆሮ 12 ላይ ብዙ ስጦታ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳለ ያስቀምጣል። የትንቢት መንፈስን ጨምሮ እነዚህ ሁሉ የመንፈስ ስጦታዎች ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ።

ኤፌ፡4፡7-13 ::

ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የምንቀበል ከሆነ የትንቢት መንፈስ ስጦታን ጨምሮ መቀበል አለብን። በእርግጥ እንደምናየው መንፈስ ቅዱስ የትንቢት መንፈስ ስጦታን የመጨረሻይቱ ቅሬታ ቤተክርስቲያን መለያ (መለኪያ) እድርጎ ያስቀምጠዋል። ዮሐንስ ራዕይ 19፡10 ስጦታንም ጨምሮ በማንኛውም ጊዜ እግዚአብሔር ስጦታ ሲሰጥ ሰዎች በአክብሮት መቀበል መቻል አለባቸው።

በመጸሐፍ ቅዱስ እና በትንቢት መንፈስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው

ኤለን ጂ ዋይት የክርስትና መሰረቱ እና መመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ታምናለች፡ : መጽሐፍ ቅዱስ የእግዝአብሔር ቃል የሐሰት ትምህርትን መለያ ብቸኛ መሳሪያ ነው። ሁሉንም ነገር በመጸሐፍ ቅዱስ መለካት አለብን። ሁሉንም ችግሮች የምንፈታው በመጸሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው።

Colporteur ministry p 125

ኤለን ጂ ዋይት ትናገራለች "(የትንቢት መንፈስ) በእግዚአብሔር ቃል ላይ በተገለጸው እውነት ላይ እንድናተኩር፣ አንዳንድ የመጸሐፍ ቅዱስ እውነቶችን በግልጽ እንድናስተውል የትንቢት መንፈስ ጽሁፍ ያግዘናል።" ኤለን ጂ ዋይት (Ellen G. white) የምታስተምረው ቤተክርስቲያን ማንኛውንም ነገር መከላከያዋ (ለትምህርቷ) ወይም ለምታደርገው ነገር ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን በመጠቀም ብቻ መሆን አለበት ትላለች።

‹‹የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው ሐሰትን የምንለይበት መሳሪያ፣ ሁሉም ነገር በመጽሀፍ ቅዱስ መመዘን አለበት ፤ ማንኛውም ትምህርት ወይም ስብከት መፈተን አለበት። የማንኛውንም ሰው ሐሳብ መቀበል የለብንም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ሳንፈትንና ሳንመረምር ምንም ነገር ልንቀበል አይገባም።

እምነትን በተመለከተ "ማንኛውም ዓይነት ችግርና ግጭት ሲፈጠር መለኮታዊ ሐይል ያለው ብቸኛ መፍትሄ የእግዝአብሔር ቃል ብቻ ነው" ።The Ellen G. white 1888 martial pp 44, 45 / Great controversy P. 595

በግልጽ ሁኔታ ስለ ትንቢት መንፈስ ጽሁፍ እና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ብላ ተናግራለች። "መጽሃፍ ቅዱስ ትልቁ ብርሃን ነው (the greater light)" የእርሷን ጽሁፍ (የትንቢት መንፈስ) ጽሁፎችን "ትንሹ ብርሃን (lesser light)" በሚል ታስቀምጣለች። ‹‹ትንሽ አትኩሮት ለመጽሀፍ ቅዱስ ስለሰጠን ጌታ ትንሹን ብርሃን (የትንቢት መንፈስን) ሰጥቷል ወደ ትልቁ ብርሃን (መጽሐፍ ቅዱስ) ሰዎችን ለመምራት። Colporteur ministry page.125

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ነብያት ጽሁፋቸው አለ። ለምሳሌ እነዚህ ነብያት ሙሴ / ኤርሚያስ / ኢሳያስ / ጳውሎስ እና ዮሐንስ እና ሌሎችም። አንዳንድ ነብያት ምንም አይነት ጽሁፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልፃፉ አሉ ነገር ግን መልዕክቶቻቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተካተዋል። ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ አራቱ የፊሊጶስ ልጆች ነብያቶች ነበሩ፡ ፡ የሐዋሪያት ሥራ 21÷9 መልእክቶቻቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተካተቱም ››

ናታን እና ጋድ

1ኛ ዜና መዋል 29÷29 / ሴኢሚያ (Shemaiah) 2ኛ ዜና መዋል ካለ 12÷15 Jasher, / Josh 10÷13 , 2 ሳሙ 1÷18 / Iddo 2 ዜና 12 ÷15 / 9÷29 Ahijoh / 2 ዜና 9፡29 / 2ኛ ዜና 20÷34

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጽሁፎቻቸው ባይካተቱም ከላይ ያየናቸው ነብያት እና የኤለን ጂ ዋይት ፅሁፎችን ጨምሮ ሙሉ ስልጣን ያላቸው ናቸው።።

የትንቢት መንፈስ አላማው ምንድነው፡፡

መፀሐፍ ቅዱስ የክርስትና መመሪያ ሆኖ ሳለ ለምንድ ነው እግዚአብሔር የትንቢት መንፈስን የሰጠው? ኤለን ጂ ዋይት በትንሹ አምስት ዋና ዋና ነጥቦችን አስቀምጣለች፡

እግዚአብሔር የትንቢት መንፈስን ለቅሬታዋ ቤተክርስቲያን የሰጠበት ምክንያት

1. ሰዎችን ወደረሱት (ወደተውት) የእግዚአብሔር ቃል ለመመለስ (to bring back to the word they neglected).

‹‹ ወደረሱት የእግዚአብሔር ቃል ለመመለስ ›› Testimony for the church, V5 p.663

የእግዚአብሔር ቃል በቂ ነው ማስተዋል ለተጋረደበት የተገለፀውን እውነት ለማረጋገጥ እንደ የኤለን ጂ ዋይት ዕሁፍ እንደ መፅሀፍ ቅዱስ ከልባቸው የሚያምኑት ሰዎች ከልባቸው ሊያምኑት ይገባል፡፡

2. በፊት የተገለፀውን እውነት ለማረጋገጥ፡፡

መፅሐፍ ቅዱስን የሚያምኑ ሰዎች ከልባቸው ሊያምኑት ይገባል፡፡ ጌታ በተሰጡት ምስክሮች ሊመክራቸው፣ ሊያስጠነቅቃቸው፣ ሊገስጻቸው እና በቃሉ አማካኝነት በተነገሩት እውነቶች ልባቸውን ሊያሸንፍ ይፈልጋል ፡፡

የኔ ዕሁፎች አዲስ ብርሐን ለመስጠት አይደለም የተሰጡት፤ የተሰጡበት አላማ ቀደም ብለው የተገለጡትን እውነቶች በልብ ውስጥ ለማተም ነው፡፡ ሰው ለእግዚአብሔር ያለው ተግባርና እርስ በርሳችን ሊኖረን ስለሚገባ ኃላፊነት በእግዚአብር ቃል ተነግሯል፡፡ ነገር ግን ጥቂቶች ናቸው ታዛዥ የሆኑት፤ አዲስ እምነት አልመጣም ነገር ግን እግዚአብሔር በምስክሮቹ ትልቁን እውነት ቀደም ብሎ የተሰጠውን በቀላሉ አስቀምጦታል፡፡ እግዚአብሔር በመረጠው መንገድ በምስክሮቹ ልባቸው እንዲነካ በኋላም ምንም ዓይነት ምክንያት እንዳያገኙ ለማድረግ ነው፡፡ **Testimony for the church.p.665**

በነገራችን ላይ የትንቢት መንፈስን ከመፅሐፍ ቅዱስ ጎን ለጎን አድርገው የሚያጠኑ ሰዎች የትንቢት መንፈስን ከመፅሐፍ ቅዱስ ጎን አድርገው ከማያነቡት ጋር ሲነፃፀሩ በመንፈሳዊ ህይወታቸው፣ በአገልግሎታቸው የበረቱ ነፍሳትን በማዳን ስራ ላይ በጣም ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ሆነው ተገኝተዋል።

3. ቅዱስ የሆነ የክርስትናን ህይወት እንድንኖር ያግዘናል።

በ1871 ላይ ኤለን ጂ ዋይት ስትናገር ፣ የትንቢት መንፈስ ዕሁፎች የተሰጡት ህይወታችንን አንደ መፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዲራመድ ለማድረግ ነው ብላለች፣ ‹‹ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር በደንብ አትተዋወቁም፤ መጽሐፍ ቅዱስን አጥንታችሁ ቢሆን ኖሮ የኔ ምስክሮች ባላስፈለጋችሁ ነበር›› ብላለች ከመጽሐፍ ቅዱስ እራሳችሁን ስላራቃችሁ እግዚአብሔር ቀለል ባለ ምስክርነት በቀጥታ በመናገር (direct Testimonies) በሐሳባችሁ ለመታዘዝ ወደረሳችሁት መፅሐፍ ቅዱስ ለመመለስ ይፈልጋል ንፁህ የሆነውን በእግዚአብሔር ቃል ህይወታችሁን እንድትገነቡ እናንተን ይማፀናል።

Selected Message p.3 ፤ 32

4. *መፅሐፍ ቅዱስን እንድናስተውል ይረዳናል*

የትንቢት መንፈስ ዕሁፍ መፅሀፍ ቅዱስን በመተርጎም (Hermenevtics) ትልቅ ሚና ይጫወታል መፅሐፍ ቅዱስን ዋነኛው የእምነታችን መሰረት በማድረግ የትንቢት መንፈስ ዕሁፎችን እንደ ተጨማሪ ብርሀን በማየት መራመድ አለብን።

‹‹እግዚአብሔር በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ቃል ገብቷል በመጨረሻ ዘመን ራዕዩን እንደሚሰጥ አዲስ እምነት ለመስጠት አይደለም ነገር ግን ህዝቦቹን ለማጽናናት እና ከመፅሀፍ ቅዱስ እውነት የወደቁትን ለመመለስ ER.p.78››። ኤለን ጂ ዋይት በግልፅ ትናገራለች የሷ ዕሁፎች መፅሀፍ ቅዱስን የሚተኩ እንዳልሆኑ።

በሌላ ቦታ እንዲህ ትላለች ‹‹እግዚአብሔር ብርሃን ሰጥቷት ነበር።።›› በጣም አስቸጋሪ ስህተቶችን ለማረም እና እውነት ምንድን ነው? የሚለውን ለመለየት።። select massage 3.p.32

5. To Shield us From Error that will come In to God Church in the Last Day (በመጨረሻ ዘመን በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ላይ ከሚመጣው ስህተት ለመጠበቅ)

ወደ መጨረሻው የአለም ፍጻሜ ስንቀርብ በጣም አደገኛ የሆኑ የሐሰት ትምህርቶች እንደሚነሱ መፅሀፍ ቅዱስ ያስተምራል፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በገለጸው በትንቢት መንፈስ ዕሁፍ አማካኝነት ቤተክርስቲያንን ከተለያዩ ስህተቶች ይጠብቃታል ።

ለምሳሌ፦ ተመሳሳይ ጾታ ጋብቻን በተመለከተ፣ አምልኮ እንዴት ይሁን፣ በሚል (በዳንስ ወይም በዘፈን) የሚለውን ሃሳብ፣ ሴቶችን በቁስነት መቀባት ፣ዘረኝነትን ፣ ፍቺን ሁለተኛ ጋብቻን በተመለከተ በእውነት ለመናገር ያለ ትንቢት መንፈስ እርዳታ እነዚህን የሐሰት ትምህርቶች መከላከል በጣም አስቸጋሪ ይሆን ነበር።

አንዳንድ ነገሮች ለምን እንደተነገሩ ሳይገባቸው ጥቅሶችን በተሳሳተ መንገድ ይጠቀማሉ (out of their context)

ለምሣሌ ፦ በ1894 ላይ ‹‹ብስክሌት እብደት ነው›› ብላ ነበር (blcycle is creazy) የተባለበት ምክንያት በዚያን ጊዜ ገንዘብ ያባክኑ ነበር፡ ብስክሌት በመግዛት አስፈላጊ የሆነውን ነገሮች በመርሳት፡፡ በዚያን ጊዜ የአምልኮ ቦታ በጣም ያስፈልጋቸው ነበር፣ ብስክሌት መግዛትን ልክ እንደ ጣኦት አምልኮ ቆጥራው ነበር፡፡ በሌላ ቦታ ደግሞ አስጠንቅቃ ነበር፣ ገንዘብ በብስክሌት ላይ በማዋል ወይም በማያስፈልጉ ነገሮች ላይ ማባከን ልክ እንዳልሆነ እንዲሁም ገንዘብን በብስክሌት፣ በውድ ልብስ፣ በማያስፈልጉ ነገሮች ላይ ማዋል ተጠያቂ እንደሚያደርግ ፡ TM FOR THE CHURCH

6- በተሳሳተ ሁኔታ መጥቀስ

በተሳሳተ ሁኔታ የትንቢት መንፈስን መጥቀስ ሌላው አደጋ ነው፡፡ ሁል ጊዜ የትንቢት መንፈስን ጥቅሶችን በመጀመሪያ ከተነገሩበት ዓላማ ውጭ ጥቅሶችን መጥቀስ፡፡

1906 የኤሌን ጂ ዋይት ጽሁፎችን በተለየ ሁኔታ አጣሞ መተርጎም አሳስቢት ስለነበረ እንዲህ ብላ ተናገራለች፡፡

‹‹በተሰጠው ብርሃን የማይራመዱ ሰዎች ከጽሁፎቼ የሚያስደስታቸውን ብቻ በመውሰድ ለእነሱ ሰበአዊ ፍርድ የሚስማማውን መልእክቶች ከተጠቀሱባቸው ዋና ዓላማ ውጭ በመለየት በሰዎች አስተሳሰብ ውስጥ በማባዛት እነሱ የሚፈልጉትን ነገር እንዲደግፍ አድርገው ያቀርቡታል›› Letter, 1906 in manuscript release #760

አንዳንድ ጊዜ በጣም መጠንቀቅ አለብን የትንቢት መንፈስን መጽሐፍ በግላቸው የሚያሳትሙ ሰዎችን ምንአልባት የራሳቸውን ሐሳብ ሊያሰፍሩ ስለሚችሉ ኤለን ጂ ዋይት ካለቻቸው ውጭ ልክ እንደቤሪያ ሰዎች መመርመር አለብን፡፡

7. Learn to discern to the underlining principles

መማር ያለብን የኤለንጂዋይት ጽሁፎች እራሳቸውን በራሳቸው እንደሚተረጉም ናቸው :: ለምሳሌ

"when many American still lived on farm, Ellen G. white suggested that school curriculum for girls. should include harnessing and driving horse. She wrote Girls … Could learn to harness and drive a horse and to the saw and the hammer as well as the take and the hoe, they would be better fitted to meet the emergencies of life" ED **p.216, 217**

ከላይ ሴቶችን የመከረችበት ዋናው አላማ በአደጋ ጊዜ በህይወት በሚገጥማቸው ነገር እንዲዘጋጁ ነው። አሁን ባለንበት ጊዜ የትንቢት መንፈስ ተሰጥቶ ቢሆን ኖሮ በህይወት ለሚገጥመን ነገሮች እንድንዘጋጅ እንዲህ ትል ነበር። የመኪና ጥገና ተማሩ፣ መንጃ ፍቃድ አውጡ፣ ሌሎች ወቅታዊ የሆኑ ነገሮችንም ትመክረን ነበር። ሰዎች በሁሉ ነገር ገጣሚዎች እንጂ ተረጂዎች እንዲሆኑ አትፈልግም፣ እራሳቸውን እንዲችሉ የሌሎችን ሸክም ማቅለል እንዲችሉ የምክርጂ ዋና ሐሳቦች ናቸው።

8. ፅሁፎጂ እራሳቸው እንዲያብራሩ መፍቅድ (Allow her writing to interpret themselves)

የኤለን ጂ ዋይት ጽሁፎች በጣም ግልጽ ናቸው አንዳንዶቹ ትንሽ ከበድ ቢሉም በብዛት ግን ለግለሰቦች የሰጠቻቸው መመሪያዎች ናቸው (instruction in her letters to individual) ኤለን ጂ ዋይት ትናገራለች የእሷ ጽሁፎች እራሳቸውን በራሳቸው እንደሚተረጉሙ ።።

‹‹የተሰጡት መልእክቶች፣ ምስክሮች እራሳቸውን በራሳቸው ይተረጉማሉ ልክ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱን በራሱ እንደሚተረጉም›› selected message 1 P.42

በሌላ አነጋገር በአንድ ቦታ ግልጽ ያልሆነ ነገር ከትንቢት መንፈስ ካነበብን ሌላ ቦታ ላይ ከጽሁፎጂ ውስጥ ሄደን ግልጽ ስላልሆነልን ነገር እናንብብ ።። የዚያን ጊዜ ሙሉ መረጃውን ማግኘት እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያልገባን ጥቅስ ቢኖር የምናደርገው ግልጽ ላልሆነልን ሀሳብ የተለያዩ ጥቅሶችን እናመሳክራለን ኢሳ 28÷10 ‹‹ጥቂት ከዚህ ጥቂት ከዚያ›› ይላል። ወይም ከትንቢት መንፈስ ፅሁፎች ውስጥ ጥቅሶች ያልገባን ነገር ካለ ከተናገረችው ምስክሮች ወይም ጽሁፎች እራሳቸውን በራሳቸው እንዲተረጉሙ መፍቀድ አለብን ።።

ኤለን ጂ ዋት ከመጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ ነች ወይ?

አንድ ጊዜ የትንቢት መንፈስ ጽሁፍ ስናጠና የትንቢት መንፈስ ከሚለው ተቃራኒ የሆነ ነገር እንረዳለን። በዚያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ነገር በተሳሳተ መንገድ አስተውለነዋል። መጽሐፍ ቅዱስ የጻፉትን ሰዎች የመራቸው መንፈስ ኤለን ጅ ዋይትንም መርቷታል (inspired) ሁል ጊዜ የትንቢት መንፈስ ጽሁፎች ከመጸሐፍ ቅዱስ ጋር ተግባብተው ይኖራሉ። ኤለን ጂ ዋይት ምግብን በተመለከተ ወደ አታክልት እና ፍራፍሬ እግዚአብሔር በመጀመሪያ በኤደን ገነት ወደ ፈጠረው ምግብ እንድንመለስ ትመክራለች።።

‹‹የምንመገበው ምግብ አትክልት ፣ ፍራፍርሬ እና ጥራጥሬን ያካተቱ ስጋ ወደ አፋችን እንዳይግባ ተፈጥሮአዊ ስላልሆነ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ሲፈጥር ወደነበረው የአመጋገብ ስርአት መመለስ አለበት›› councel food and diet P 380

‹‹ለራሳችን ሲባል የቅሬታዋ ቤተክርስቲያን ስጋ ሻይ እና ቡና ሌሎችም ጉጂ የሆኑ ምግቦችን ማስወገድ አለባት ብዙ ነገሮች አሉ እነዚህን ልንተካ የምንችልበት፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ንጹህ የሆነውን ስጋ እንድንበላ ይፈቅዳል ፋሲካ ሲያደርጉ በግ ታርዶ ነበር፡፡ (ዘሌዋዊያን 12) እንዲሁም ኢየሱስ አሳ በልቷል ከትንሳኤ በኋላ (ዮሐንስ 21) ስናነብ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስጋ የተበላበት ቦታ ስላለ የትንቢት መንፈስ ስጋ አትብሉ ትላለች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ትጋጫለች ማለት ነውን? አይደለም!! እንደዚህ የምንል ከሆነ በትክክል የትንቢት መንፈስ ጹሁፎችን በሚገባ አላነበብንም ማለት ነው፡፡

በእርግጥ ኤለን ጂ ዋይት ስጋ መብላትን በምንም መንገድ አታበረታታም ነገር ግን በማንኛውም ሁኔታ አታስተምርም በአንዳንድ ምክንያቶች (ችግሮች) ተነስተን ስጋ ብንበላ አትቃወምም ፣ ሰዎች በጣም ጤናማ የሆነ ምግብ እንዲመገቡ ትገፋፋለች ፡፡ በአንዳንድ አገሮች ላይ አታክልት፣ ፍራፍሬ ጥራጥሬ፣ የተለያዩ ኦቾሎኒዎች ባሉበት አገሮች ላይ እንዲህ ብላ ጽፋለች ‹‹ስጋ መብላት ለእግዚአብሔር ሰዎች ትክክል አይደለም›› testimonies for the church page 159.

የቤተክርስቲያን አባላት ስጋ መብላት ማቆም አለባቸው ስትል ስጋ መብላት ኀጥያት ስለሆነ አይደለም ነገር ግን ጤናማ ስላልሆነ (ለጤናችን በጣም ጎጂ ስለሆነ ነው)፡፡ Manuscript releases 5 401

‹‹እንሰሳት ከመቼውም ጊዜ በላይ በበሽታ እየተጠቁ የመጡበት ወቅት ነው፣ እሩቅ አይደለም ስጋ አድቬንቲስቶች ብቻ ሳይሆኑ ዓለም እራሱ መብላት ያቆማል፡፡ ጤናማ እና ህይወታችንን በጤንነት የሚያቆይ ምግብ ማዘጋጀት አለብን ስለዚህ ማንኛውም ሰው ሥጋ መብላት የለበትም›› Testimony for the church 7:124

በአለማችን ላይ በጣም ችግር እየሆነ የመጣው የእንስሳት በሽታ መጨመር ነው፡፡ እንዲሁም የተለያዩ መረጃዎች አሉ ሰዎች አትክልትን እና ፍራፍሬን እንዲመገቡ የሚመክሩት፣ ማንኛውም ሰው ሥጋ መብላት የለበትም ኤለን ጂ ዋይት መፅሐፍ ቅዱስ የሚለውን አትቃወምም በዚህ ጉዳይ ላይ ይልቁንም መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ለሰውነታችን እንድንጠነቀቅ ትመክረናለች ምክንያቱም ሰውነታችሁ የህያው እግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ ስለሆነ ፡፡ 1ቆሮ 3፡16.17 / 6፡19

እስቲ የኤለን ጂ ዋይትን የህይወት ልምድ እንፈትን

መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚለው በመጨረሻ ጊዜ ሐሰተኛ ነብያት እንደሚነሱ ያስተምራል። ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ነበር ‹‹ሀሰተኛ ክርስቶሶች ሐሰተኛ ነብያቶች ታላቅ ተአምር ምልክት ማታለያዎች ያደርጋሉ ቢቻላቸው የተመረጡትን እስኪያስቱ ድረስ›› ማቴ 24፡24 ። በጣም ጥቂት መመዘኛዎች አሉን ማንን እውነተኛ ነብይ ብለን እንደምንቀበል የሚያስችሉን። ‹‹ወደ ህግና ወደ ምስክር ሂዱ›› ኢሳ 8፡20 ይህንን ዋነኛ መፈተኛ ለኤለን ጂ ይዋትም ማዋል እንችላለን፣ እሷ በአሁኑ ጊዜ ወደ 45 ቮሊዮም መፅሀፍቶችን ፅፋለች እነዚህ መፅሀፍቶች የክርስቶስን ህይወት ያጠቃልላሉ፣ የመፅሐፍ ቅዱስን መመሪያዎችን ይዘዋል፣ በብዙዎች መቶ የሚቆጠሩ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ጠቅሳ ተጠቅማለች።

ስለ ሰባተኛው ቀን ሰንበት ኤለን ጂ ዋይት የተናገረችው

ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር ሰንበትን የሰጠው በኤደን ገነት ነበር። ዘፍ 2:2÷3 እስራኤሎች ከግብፅ ከለቀቁ በኋላ እግዚአብሔር እንደገና ህጉን በሲና ተራራ ላይ በመስጠት ሰንበትን አስታውሷቸዋል ዘፀ 19÷20 ከዚያ በኋላ ለዘመናት በእስራኤል ሰዎች ሲጠበቅ ቆይታል።

የሰንበትን ትዕዛዝ በማፍረሳቸው ነበር ወደ ባቢሎን የተማረኩት ኤር 17÷27 ከባቢሎን ከተመለሱ በኋላ የሰንበት ተሐድሶ አድርገው ነበር። ነህምያ 9÷14 / 10÷31 / 13 15÷22፡ :

ኢየሱስ እራሱ በምድር በነበረበት ወቅት ሰንበትን ይጠብቅ ነበር። ሉቃ 4። ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ለሁለተኛ ጊዜ ምድር ላይ በሰንበት ምክንያት የሚመጣ ታላቅ ፈተና ይሆናል። ይሄ በዳንኤል እና በዮሐንስ ራዕይ መፅሐፍ ላይ በትንቢት መልዕክት ተቀምጧል፡ :

ዳን 7 24÷25 / ዮሐን ራይ 13 1÷18

ለቅሬታዋ ቤተክርስቲያን ሰንበትን ወደ ነበረበት ቦታ መመለስ ከተልዕኮዎችዋ ዋነኛው ክፍል ነው። ምክንያቱም ሰንበትን እግዚአብሔር ሲሰጥ እርሱን በእውነት ለሚያመልኩት ሰዎች ምልክት እንዲሆን ነው ህዝ 20 ÷ 20 ። መፅሐፍ ቅዱስ ሲናገር በአዲሲቱ ምድር ሰንበትን እንደምንጠብቅ ማየት እንችላለን ኢሳ 66÷23። በትንቢት መንፈስ ፅሁፍ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሰንበትን አስፈላጊነት ፣እንዴት መጠበቅ እንዳለብን በደንብ ተነግሮናል ።

‹‹ሰንበት የተቋቋመው በኤደን ገነት ነው ምድር ስትፈጠር ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የቀጠለ ነው›› Patriachs and prophet's page. 47, 48

‹‹ በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ህጉን ሲሰጥ ሰንበትን በዚያው አብሮ ሰጥቶ ነበር ። እስራኤላውያን ከዚህ በፊት ስለ ሰንበት ያወቁ ነበር ይህ የመጀመሪያቸው አይደለም፣ በሲና ተራራ ላይ ሳይሰጣቸው በፊት ስለ ሰንበት እውቀቱ ነበራቸው›› DA Page 283

‹‹ሰንበት የታማኝነት መለኪያ ነው›› GC Page 453

ስለ ኢየሱስ ዳግም ምፅአት ኤለን ጂ ዋይት የተናገረችው

ኢየሱስ ዳግመኛ ተመልሶ እንደሚመጣ መፅሐፍ ቅዱስ በግልፅ ይናገራል ዮሐ14÷1 / ሉቃ 21÷27 / ማቴ 16÷27 / ሉቃ 9÷26 ። ሀጥያተኞች ግን ለመደበቅ ይሞክራሉ ዮሐን ራይ 6 ፥ 15-17፡ ፃድቃን አንድ ሺህ አመት ከክርስቶስ ጋር ከነገሱ በኋላ ወደዚህ ምድር ይመለሳሉ፤ ይህችንም ምድር ይወርሳሉ ዮሐ ራዕይ 21÷2-20 ‹ነጥያተኞች ላይ ደግሞ እንደሚፈርድባቸው ቃሉ ይናገራል፡፡ ይሄን ለመረዳት ታላቁ ተጋድሎ የሚለውን የኤለን ጂ ዋይት መጽሐፍ ላይ መረጃ ያገኛሉ ።

ኤለን ጂ ዋይት ስለ ክርስቶስ በክብር መምጣት ምን አስተምራለች?

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የገባው ቃል ‹‹ተመልሼ እመጣለሁ ወደ እኔ እወስዳችኋለሁ፣ እሱን የሚወዱት እና የሚጠብቁት በክብር ያገኙታል፣ የሞቱት ፃድቃን በክብር ይነሳሉ በህይወት ያዩታል፣ ከእርሱ ጋር ይነጠቃሉ››፡፡ AC Page, 334

"ምድራችን ትልቅ መደናገጥ ውስጥ ትወድቃለች የእግዚአብሔርን ልጅ ድምጽ ስትሰማ የሞቱትን ፃድቃን በሚጠራበት ጊዜ ለጥሪው መልስ ይሰጣሉ ፃድቃን የማይሞት ሥጋ ለብሰው ይነሳሉ" 1ቆሮ 15÷ 55-56 ። እንዲህ ይባላል "ሞት መውጊያህ የት አለ መቃብር ሆይ ሐይልህ የት አለ" ። ‹‹ምድር ሁሉ ልክ እንደ ጠፋ በረሀ ሆና ነበር ከተሞች፣ መንደሮች በመሬት መንቀጥቀጥ ጠፍተው ነበር፣ ዛፎች ተነቅለው ነበር፣ ታላላቅ ድንጋዮች ወደ ጥልቁ ባህር ገብተው ነበር፣ ተቆርጠው በምድር ላይ ተበታትነው ነበር ፣ከተነቀሉበት ቦታ ላይ ምልክት አልነበረም›› GC Page 657

ሶስተኛው መፈተኛ

‹‹በፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ›› ማቴ 7፥15-20

ኤለን ጂ ዋይት አገልግላ ካለፈች ብዙ ዘመን አልፏል ከሞተችም እረጅም ጊዜ ነው። ስለዚህ ስለ ህይወቷ እና ስለ ስራዋ ፍሬ ለመፈተን በጣም አመቺ ነው ።

የኤለን ጂ ዋይት ህይወት

ኤለን ጂ ዋይት ከሞተች ከጥቂት ጊዜያት በኋላ አንዳንድ ጋዜጦች እንዲህ እያሉ ዘግበው ነበር በካሊፎርኒያ ከተማ ሲንት ሄሌና - በሚባለው ቦታ ለ15 አመት በዚያ አካባቢ ኖራ ነበር፡፡

‹‹The Good Samaritan will surely be greatly missed her reward will be commensurate with the great good she has done››

Saint Helena, California, store, July 23, 1915, an article in the Detroit new, tribune commented

‹‹Mrs. White was deeply seriously and none who know her ultimating had any debit as to her society›› July 25, 1915

የኤለን ጂ ዋይትን የግል ህይወት የሚያውቁ ሰዎች እንዲህ ብለው ነበር

‹‹a noble Christian woman gone›› Comment of D.H can right See arthor w. Spalding, captains of the host Page 581

ኤለን ጂ ዋይት የሰራችውን ስራ ማየት ከፈለግን ዞር ብለን የሰባተኛ ቀን ኢድቬንቲስት ቤተክርስቲያንን አነሳስ እና አሁን ያለችበትን በፀጋ የተሞላ አገልግሎት ማየት አለብን፡፡ እግዚአብሄር በየጊዜው በሚሰጣት ህልም እና ራዕይ ኤለን ጂ ዋይት ያደረገችውን ነገር እስቲ በአጭሩ እንመልከት፣ ቤተክርስቲያንን እየመከረች፣ እየገሰፀች እየመራች እዚህ አድርሳታለች፡፡

1. የቤተክርስቲያን ዶክትሪን እንዲመሰረት እረድታለች፡፡
2. ሰዎችን ከሐሰት ትምህርት እና አክራሪነት መልሳለች፡፡
3. ቤተክርስቲያንን እንዲመሰረት ትልቅ አስተዋፆኦ አድርጋለች፡፡
4. ችግር ሲነሳ ቤተክርስቲያን ካለችበት ችግር እንድትወጣ ትረዳ ነበር፡፡
5. የወደፊቱን እቅድ ትመራ ነበር (እግዚአብሄር በሚሰጣት መመሪያ መሰረት) ፡፡
6. መፅሐፍ ቅዱስ እንዲጠና ታበረታታ ነበር፡፡

በህይወቷ እየመራች ታሳይ ነበር፡፡ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ያላትን ትምህርት ቤቶች ፣ሆስፒታሎች ፣ የቲዎሎጂ ትምህርት ቤቶች ፣የእርዳታ ድርጅቶች በመላው ዓለም ላይ የአድቪንቲስት ቤተክርስቲያን እውነት መስፋፋቱ እንዱ

7. ከፍሬዎችዋ ዋነኞቹ ክፍሎች ናቸው። በፍሬያቸው ታውቋችዋላችሁ የሚለውን ሐሳብ ሙሉ ለሙሉ የምታሟላ ነብይ ነች፣ በነብዩ የተነገረው በሚፈፀምበት ጊዜ ያ ነብይ እግዚአብሄር የላከው እንደሆነ ይታወቃል።

ስለሚመጡት የወደፊት ችግሮች የተናገረቻቸው ትንቢቶች

‹‹ ወጣቶች እግዚአብሄርን ከልባቸው መፈለግ አለባቸው፣ መከራ እየመጣ ነው። ለሚመጣው ችግር በንስሀና በእምነት ወደ አምላካችን እግዚአብሔር መመለስ አለብን። ይህችን ምድር ያንቀጠቅጧታል፣ በኛ ላይ ብዙ ችግሮች ይደርሳሉ፣ ብዙ መርከቦች ወደ ጥልቅ ባህር ይሰጥማሉ፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የሰው ልጆችን ህይወት ይቀጥፋል። የሰደድ እሳት ሳይታሰብ በልዩ ልዩ ቦታዎች ላይ ይሆናል። የሰው ልጅ ጥረት እንኳን ሊያጠፋቸው የማይችል እሳት ብዙ መኖሪያዎችን ያወድማሉ፣ የተለያዩ የባቡር አደጋዎች ይሆናሉ፣ ሁከት ሞት፣ ያለምንም ማስጠንቀቂያ በጉዞ ላይ ይደርሳሉ ›› ። Message to your people P.89.9

ይህን የተናገረችውን ትንቢት ለመመልከት የመጀመሪያውን እና የሁለተኛውን የአለም ጦርነት ማየት ብቻ ይበቃል። ከዚህ በኃላ የደረሱትን ውድመቶች ሳንቆጥር እንኳን።

እንደምናውቀው እንግሊዝ እና አሜሪካ አብረው ነበሩ በሁለተኛው የአለም ጦርነት 4770 መርከቦች አጥተው ነበር። በአጠቃላይ 21.000.00 (ሃያ አንድ ሺህ) ቶን መርከቦች ወድመው ነበር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀርመን ፣ጣሊያና ጃፓን ያጡትን በመርከቦቻቸው ላይ የደረሰውን ውድመት አያካትትም፣ የሰው ህይወት በብዙ ሚሊዮን ጠፍቷል።

የሁለቱን የዓለም ጦርነቶች ዘገባዎች ማየት ከቻልን ምን ያህል ሰው እንደጠፋ እናያለን፣ ያለቁት ሰዎች በሁለቱም ጎራ በኩል በጣም ብዙ ናቸው ። በጦርነቱ የሞቱት ወታደሮች እና የሰላማዊ ሰዎች ህይወት ውድመት ደርሷል።

በእሳት አደጋ በአሜሪካ አገር ውስጥ $188, 705, (አንድ መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ አምስት) በላይ፣ድምሩ $815, 134, 000 (ስምት መቶ አስራ አምስት ሚሊየን አንድ መቶ ሰላሳ አራት ሺህ) በላይ ወድሟል፣በ1909፣ ምንም አይነት ማብራሪያ አያስፈልገውም በባቡር ግጭት በአውሮፕላን አደጋዎች ምን ያህል ሰው እንደሞተ መገመት ይቻላል። ይህ የየቀኑ ተግባር ሆኗል። በአሁኑ ጊዜ እንደዚህ አይነት ድርጊቶች እንደሚከሰቱ በትንቢት ተነግሮ ነበር። source prophet among you book.

አራተኛው መፈተኛ

‹‹ሁሉም መንፈስ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ መቀበል መቻል አለበት›› 1ዮሐ. 4÷2 ::

ኤለን ጂ ዋይት በኢየሱስ ህይወት እና ስለ አገልግሎቱ ከአባቱ ጋር ከዘላለም ጀምሮ አብሮ እንደነበር ፅፋለች፡፡ ስለ ሰማያዊው አገልግሎት እና ስለ ዳግም ምፃቱ ሰፋ ባለ መልኩ ፅፋለች፡፡

ይሄን ለመረዳት የዘመናት ምኞት የሚለውን መፅሀፍ ማንበብ በቂ ነው፡፡ የዘመናት ምኞት የሚለው መፅሐፍ በራሱ የደህንነት ሳይንስን የገለፀችበት መጽሐፍ ነው፡፡

1. ስለ ክርስቶስ መወለድ
2. ስለ አገልግሎቱ
3. በምድር ስለነበረው ህይወት
4. ስለ አሳለፈው መከራ
5. ስለ ስቅለቱ
6. ስለ መነሳቱ
7. ወደ ሰማይ እንዳረገ
8. ስለ ዳግም ምፃቱ በሰፊው የፃፈችበት መፅሐፍ ነው፡፡

ይህን ለማወቅ የሷን መፅሀፍቶች በበቂ ሁኔታ ማንበብ አለብን፡፡ የዘመናት ምኞት፣ የተራራው ስብከት፣ ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ መንገድ የሚሉትን ብናነብ በቂ መረጃን እናገኝለን ::

‹‹ከዘመናት ጀምሮ ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ይኖር ነበር እኩልም ነው ›› DA የዘመናት ምኞት

‹‹ሀኪያት የማያውቀው ኢየሱስ የኛን ቦታ ወሰደ›› The Ministry of healing P.71

‹‹በአይምሮአችን መጽናናት አለብን ታላቅ ሊቀ ካህን በሰማይ እንዳለን ስለእኛ የሚማልድ›› Testimonies V.4 Page 530

"የተባረከውን የኢየሱስ ዳግም ምፅአት እውነት ለዚህ ህዝብ መቅረብ አለበት"Testimonies V.6.P.406

"የመፅሐፍ ቅዱስ ዋናው ሀሳቡ የኢየሱስ ደግሞ ምጽአት ነው" G.C P 299

"Christ was treated as we deserve, that we might be treated as he deserves……He suffered the death which was ours, that we might receive the life which was His" DA Page 28

መደምደሚያ

አራቱ የመፅሀፍ ቅዱስ የነብያት መፈተኛዎች

1. ወደ ህግ እና ወደ ምስክር መሄድ፡፡
2. በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፡፡
3. ነብዩ የተናገረው ነገር መፈፀም አለበት፡፡
4. ነብይ ነኝ የሚል ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ መቀበል አለበት፡፡

በትክክል የነብይነት መለኪያ ተጠቅመን ኤለን ጂ ዋይትን ስንፈትን ሁሉንም የመፈተኛ መስፈርቶች በትክክል ታልፋለች፣ ስለዚህ እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ለቅሬታዋ ቤተክርስቲያን የሰጣት ነብይ እንደሆነች ማመን አለብን፡፡ መፅሀፍ ቅዱስ በእውነተኛ ነብያት እመኑ ይላል፡፡ ‹‹በአምላካችሁ በእግዚአብሔር እመኑ ትፀኑማላቹ በነብያቱም እመኑ ሁሉም ነገር ይሳካላችኋል» ይላል፡፡ 2ዜና.20፡20

የነብያት እና የኤለን ጂ ዋይት መልዕክቶች

እግዚአብሔር መልዕክቱን ለነብያት በሚሰጥበት ጊዜ የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀም ነበር ዕብ 1፡12

1. የነብዩን ባህሪ ተመርኩዞ መልዕክቱን ያስተላልፍ ነበር

ለምሳሌ ...ነብዩ ዮናስን መጥቀስ እንችላለን ፡፡

2. የሰዎችን ፍላጎት ተከትሎ ለነብዩ መልዕክት ይሰጥ ነበር፣

የኤርሚያስን እና የህዝቅኤልን ታሪክ ማየት ይቻላል ፡፡

3. ሁኔታዎችን ተከትሎ ለነብያት መልዕክት ይሰጥ ነበር

ለምሳሌ የዳንኤልን ትንቢት ማየት ይቻላል ፡፡

ኤለን ጂ ዋይት እንዴት ነበር ህልም የተሰጣት?

1. በምትፀልይበት ሰዓት

‹‹በምፀልይበት ጊዜ የእግዚአብሔር ሐይል በኔ ላይ መጣ ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ በማይታወቅ ሁኔታ በብርሃን የተከበብኩ ይመስለኝ ነበር ከምድር ከፍ ከፍ እያልኩ እሄድ ነበር፡፡ አድቬንቲስቶችን ለማየት ሞከርኩ ላገኛቸው ግን አልቻልኩም አንድ ድምፅ እንዲህ አለኝ እንደገና ተመልከቺ ትንሽ ከፍ አድርገሽ እዩ›› አለኝ፡፡ Testimonies Vol 1 P. 58

ነብዩ ራዕይ በሚያይበት ጊዜ ሙሉ ለሙሉ አዕምሮው በምድር ላይ የሚያደርገውን ነገር አያውቅም (unconscious) ፣ ኤለን ጂ ዋይት ከምድራዊ ነገር ላይ አይምሮዋ ተነስቶ

ወይም በዙሪያዋ የሚደረገውን ነገር አታውቅም ነበር። ምሳሌ ህዝ 8÷3 / 2ቆሮ 12 ፥ 2÷4

ሌሎች ሰዎች ደግሞ ለራዕይዋ የዐይን ምስክርነት የሰጡ ነበሩ።

1. ባለቤቷ ሚስተር ጀምስ ዋይት የመሰከረው ምስክርነት ይገኝበታል።
2. ብዙ ራዕዮቿ የተሰጧት በተለያዩ ጉባኤዎች መካከል ነበር።
3. ባሳ የሰጠው ምስክርነት እና ሌሎች የሰጡት ምስክርነት ተመሳሳይ ነበር።
4. አትተነፍስም ነበር ራዕይ እያየች ከ15 ደቂቃ እስከ 3 ሰዓት ድረስ ትቆይ ነበር።

ብዙ ጊዜ ደረቷን እየተጫኑ ይፈትኗት ነበር ትተነፍስ ወይም አትተነፍስም እንደሆነ አፏን እና አፍንጫዋን በመዝጋት ትተነፍስ ወይም አትተነፍስም እንደሆነ ለማረጋገጥ ይሞክሩ ነበር።

መደምደሚያ

I. ሁልጊዜ ራዕይ ከማየቷ በፊት እግዚአብሔር በመሐል እንዳለ ይሰማት ነበር እሷ ብቻ ሳትሆን ሌሎች አብረዋት ያሉት ሰዎች ሁሉ ይሰማቸው ነበር።
II. ኤለን ጂ ዋይት ልክ ራዕይ ማየት ስትጀምር እንዲህ ትል ነበር ‹‹ክብር ክብር፤ ክብር ለእግዚአብሔር ሶስት ጊዜ በማከታተል ታሰማ ነበር››።
III. ከዚያ በኋላ አምላካዊ ጥንካሬ ይከተላት ነበር።
IV. በዚህ ጊዜ ትክክለኛ የሆነ ነገርን ታወራለች።
V. አይኖቿ ራዕይ በምታይበት ጊዜ የተከፈቱ ነበሩ፣ ልክ ከሩቅ የሆነ ነገር የምታይ ይመስል ነበር።
VI. ራዕይ በምታይበት ጊዜ አንድ ቦታ አታቆምም ነበር ልትቀመጥ ትችላለች እንደገናም ደግሞ በክፍሉ ውስጥ ትራመድ ነበር።
VII. የልብ ምቷ ግን ትክክለኛ ነበር (normal) የፊቷ ከለረም ተፈጥሮአዊ ነበር ምንም አይነት ሁከት በአካሏ (በአተነፋፈስ ስርአቷ ላይ) አይታይም (Disturbance in the circulatory system).

ኤለን ጂ ዋይት ያየችውን ራዕይ ስትፅፍ ወይም ስትናገር ሁልጊዜ የመንፈስ ቅዱስ አመራር ቢመራትም እንኳን ስትገልፀው ግን የራሷን ቃላት ተጠቅማ ነው የምትገልፀው (የምትናገረው)።

‹‹እኔ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ ነበር የተደገፍኩት ያየሁትን ነገር ለመፃፍ ልክ እንደተቀበልኩት ምንም ሳይጨመር ለማስተላለፍ ለመግለፅ የተጠቀምኩት የራሴን

ቃላት ነው፡፡ መልአኩ በቀጥታ ከተናገረኝ ውጪ ሁልጊዜ ይሄንንም ደግሞ በትምህርተ ጥቅስ አስቀምጨዋለሁ መልአኩ በቀጥታ የተናገረኝን›› Ellen G. White in review and herald Oct. 8, 1867

‹‹ለሰዎች በብዛት በምንናገርበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በሐይል በኔ ላይ ይመጣል፡፡ በህይወቴ በኑሮዬ እንዲሁም በባህሪዬ የተለየሁ ነበር፡፡ ስህተቶችን፣ አደገኛ ነገሮችን እመለክታለሁ ያየሁትን ነገር ለመናገር እፈራ ነበር›› Testimonies vol 5, P 698

በአንድ ምሽት እግዚአብሔር መመሪያ በምልክት (Symbol) ሰጠኝ ፣ ከዚያ ያንን ደግሞ ምልክቱን አብራራልኝ የትርጉሙን ቃል ሰጠኝ፣ ለህዝቡ ለማስተላለፍ እምቢ ማለት አቃተኝ የክርስቶስ ፍቅር እና የነፍሳት ፍቅር ግድ ይለኝ ስለ ነበር ፡፡ Ellen G. White Manuscript 22, 1890

እግዚአብሔር በሰጣት መልዕክት ሽክም እንደሚሰማት በትክክል ለህዝቦቹ ለማስተላለፍ ከተናገረችው ከባፈችው ዕሁፎች ማየት እንችላለን፡፡

የምታየው ህልም ሁሉም በአንድ አይነት መንገድ አልነበረም የታያት አንዳንዶቹ ልክ ሰው ቴሌቪችዮን ቁጭ ብሎ እንደሚያየው ያለፈውን ሁናቴ እና የወደፊቱን ታይ ነበር፡፡

መልዕክቷ የተላለፍበት_መንገድ

በስብከት (sermon) መልክ

በደብዳቤ (letters / Interview)

በቃለ መጠይቅ በፅሁፍ (Article)

የግል አስተያየት መልክ (Personal Statement) ነበር ፡፡

መፅሐፍ ቅዱስ እና የትንቢት መንፈስ

‹‹...በጣም ትንሽ አትኩሮት ነው ለመፅሐፍ ቅዱስ የተሰጠው እግዚአብሔር ትንሹን ብርሃን ሰጥቷል፤ ወንዶችን እና ሴቶችን ወደ ትልቁ ብርሃን እንዲመራ ...›› E.G White review and herald Jun 20, 1903.

ኤሌን ጂ ዋይት ስለራሷ መፅሐፍት ስትናገር ትንሹ ብርሃን ነው ትላለች፣ እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ ትልቁ ብርሃን(መፅሐፍ ቅዱስ) የሚመራበት፣ ሁለቱንም ብርሃን በትክክል

መጠቀም ከፈለግን መፅሐፍ ቅዱስ እና የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን ቦታቸውን ማወቅ አለብን፣ ኤሌን ጂ ዋይት ስለዚህ ነገር ምን ትላለች፡፡

‹‹ መፅሀፍ ቅዱስ ሙሉ ስልጣን እንዳለው መቀበል አለብን የማይሳሳት የእግዚአብሔር ፈቃድ መገለጫ ነው ፣ የባህሪ መለኪያ ነው ::

የትንቢት መንፈስ ፅሁፍ ቦታው

መፅሀፍ ቅዱስ እና የትንቢት መንፈስ ፅሁፎች የተለያዩ ተልእኮ ነው ያላቸው ነገር ግን ለእግዚአብሔር ህዝብ የሚሰጡት አገልግሎት አንድ ነው፡፡ እሱም የእግዚአብሄርን ፍቃድ ለማስተላለፍ ወይም ለመግለፅ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ትዕዛዝና በኢየሱስ ምክር ሰዎችን እየመራ ያወጣል በአለቱ ላይ በእምነት ሊመሰርታቸው፡፡

መፅሐፍ ቅዱስ እና የትንቢት መንፈስ ግንኙነታቸው

መጨረሻው እየቀረበ ሲመጣ የመጨረሻውን ማስጠንቀቂያ ለዓለም የመስጠት ስራ ይቀጥላል፡፡ ወቅታዊው እውነት በጣም ትልቅ ዋጋ ያለው ይሆናል ንፁህ እና ትክክለኛ የሆነ አስተሳሰብ ይኖራቸዋል በተሰጡት ምስክሮች ላይ የእግዚአብሔርን ምህረት በሶስቱ መልአክት መልዕክት ከመጀመሪያው ጀምሮ እናገኛቸዋለን፡፡

እውነተኛ ጥቅም እና እውነተኛው በረከት የሚመጣው የትንቢት መንፈስ ጽሁፍ ለቤተክርስቲያን እንደተሰጠ ለሚቀበሉ ደግሞም በትንቢት መንፈስ ጽሁፎች ስራውን እንደሚፈፅም በሚያምኑ ሰዎች ላይ ነው፡፡ እግዚአብሔር የትንቢት መንፈስን የሰጠበት ዋና አላማው የእግዚአብሔር ህዝቦች አትኩሮት ለመፅሐፍ ቅዱስ ስላልተሰጡ ነው፡፡ በጣም ቀለል ባለ መንገድ በቀጥተኛ ምስክርነት የህዝቡን አትኩሮት ወደ መፅሐፍ ቅዱስ ለማድረግ ነው ::

የኤለን ጂ ዋይት ጽሁፎች በመፅሀፍ ቅዱስ መለካት አለባቸው፡፡

‹‹ከመፅሐፍ ቅዱስ በላይ እራሱን ከፍ ለማድረግ ለሚሞክር፣ መንፈስ ቅዱስ አይሰጥም ወይም አይወርድለትም :: ሁሉም ዓይነቶች ትምህርቶችና ልምዶች በመፅሐፍ ቅዱስ መለካት እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ ይናገራል፡፡ ‹‹የትንቢት መንፈስ ጽሁፎች የተሰጡት መፅሀፍ ቅዱስን ለማሳነስ ሳይሆን ከፍ ከፍ ለማድረግ ነው›› J.Church V.S P.665

‹‹ወንድሞች ሆይ የእምነታችሁ መመሪያ እና ልምድ መፅሐፍ ቅዱስ ይሁን በእግዚአብሔር ቃል ይፈረድብናል›› ኤለን ጂ ዋይት ወደ መጨረሻዎቹ የህይወቷ ክፍል ወይም በእርጅና

ምክንያት ለረጅም ጊዜ ስታገለግልበት ከነበረው አገልግሎቶቿ ስትታቀብ በስብሰባ ላይ ለነበሩት ሰዎች የተናገረችው የመጨረሻ ቃል ይህ ነበር ፣ወንድም እና እህቶች “I commend unto you this book” ‹‹ይሄንን መፀሐፍ ቅዱስ እንድታነቡት እመክራችኋለሁ›› ::

<u>የትንቢት መንፈስ ፅሑፍ የተሰጠበት ዋና አላማው</u>

1. **መጽሐፍ ቅዱስን ከፍ ለማድረግ**
   1 - የኔ ጽሁፎች መፅሐፍ ቅዱስን የሚያሳንሱ አይደሉም፤ ነገር ግን ከፍ የሚያደርጉ ናቸው።።
   2 - ውድ አንባቢያን መጽሐፍ ቅዱስን የእምነታችሁ መረጃ እና ልምድ እንዲሆን አደፋፍራችኋለሁ ይህን አባባል በፃፈቻቸው ጽሁፎች ሁሉ ላይ የምታንፀባርቀው ነው።።

3 - የሰዎችን አዕምሮ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መምራት ነው፣ የኤለን ጂ ዋይት ፅሁፎችን ብንመለከት በእግዚአብሔር ቃል ጥቅሶች የተሞሉ ናቸው።።

4 - ወደ ተረሱት እውነቶች የሰዎችን አዕምሮ መምራት

ብዙ ጊዜ ስትፅፍ የትንቢት መንፈስ ፅሁፎች ለምን እንደተሰጡ ስትናገር ‹‹ሰዎች መፅሐፍ ቅዱስን ማንበብ ስለረሱ ወይም ስለዘነጉ ነው እግዚአብሔር በጣም ቀለል ባለ ምስክርነት ሰዎችን ሊገናኝ የፈለገው››

5 - በፊት የተገለፁትን እውነቶች መልሶ ለማጠናከር

‹‹የትንቢት መንፈስ ጽሁፎች አዲስ ብርሃን አይደሉም ነገር ግን በፊት የተገለፁትን እውነቶች በሰዎች ልብ ውስጥ ለማተም ነው ››

6 - አዕምሮን ለማነቃቃት።።

7 - እውነቱን ለማብራራት

‹‹በትንቢት መንፈስ ፅሁፎች እግዚአብሔር አዲስ እውነት አይደለም የሰጠው በፊት የነበሩትን አውነቶች በይበልጥ አብራራቸው›› Testimonies V.5 p 665

2- መመሪያዎችን ለማስተላለፍ

‹‹ቀጥተኛ የሆነ መመሪያ (principle) እንዲወጣ በንግግር እና በጽሁፍ ተመርቼ ነበር ››

በማጠቃለያ እነዚህ የትንቢት መንፈስ ፅሁፎች ለምን እንደተሰጡ ለማወቅ

1. የሰዎችን አዕምሮ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ለማምራት
2. መጽሐፍ ቅዱስን ሰዎች እንዲያስተውሉ

3. በህይወታቸው መጽሐፍ ቅዱስን እንዲተረጉሙ ለማድረግ ነው ።

በብሉይ ኪዳን የነበሩት ነብያት ሲያደርጉት የነበረውን ስራ በተለያየ መንገድ መክፈል ይቻላል ። እንደ እግዚአብሔር ሆነው ይናገራሉ፣ የእግዚአብሔርን ዓላማ ይገልፃሉ ፣ መሪዎችን ይመራሉ፣ ያጠነክራሉ፣ ሰዎች ታማኞች እንዲሆኑ ያበረታቱ ፣ክፋትን ይቃወሙ ነበር ። ኤለን ጂ ዋይትም ህይወቷን በሙሉ ያሳለፈችው ተመሳሳይ ስራ በመስራት ነበር፡ ፡

<u>ለምሳሌ</u>

1. **ስለ እግዚአብሔር ትናገር** ነበር።

"በራሴ ጥበብ የለኝም እኔ በእግዚአብሔር እጅ ያለሁ መሳሪያ ነኝ እሱ ያለኝን ስራ ለመፈፀም የፃፍኳቸው እና የተረኳቸው መመሪያዎች እግዚአብሔር የሰጠው ብርሃን መገለጫዎች ናቸው" Testimonies V.5 p.691

2. **የእግዚአብሔርን ህዝቦች ማነቃቃት**

‹‹ ከፊታችን በጣም ትልቅ ስራ ይጠብቀናል። አንዳንድ ሰዎች ወደ ቻይና እና ወደ ሌላ ቦታዎች እንዲሄዱ ይፈልጋሉ እውነቱን ለማወጅ በመጀመሪያ ግን እራሳቸው የበቁ የተማሩ መሆን አለባቸው እና ተሞክረው (ተፈትነው) ያለፉ መሆን አለባቸው››

3. **መሪዎችን ትመራ ታበረታታ ነበር ።**

አንዳንድ ጊዜ በቤተክርስቲያን የሐሰት ትምህርት በሚነሳበት ወቅት ኤለን ጂ ዋይት እንዴት አድርገው መሪዎች ይዜንን ችግር መፍታት እንዳለባቸው ትመክራቸው ነበር ።

4. **ሰዎች ታማኞች እንዲሆኑ ታበረታታ ነበር**

‹‹ወንድሞቼ እና እህቶቼ ለክርስቶስ ዳግም ምፅአት እንድትዘጋጁ እገፋፋችኋለሁ›› Testimonies V.9 page 285

የትንቢት መንፈስ ጽሁፎች ስራን ብንመለከት ሰዎች በአገልግሎታቸው፣ በመንፈሳዊ ህይወታቸው ሁሌ ታማኞች እንዲሆኑ ትገፋፋቸው ነበር።

የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን በአሁን ዘመን ማዋል እንችላለን።

በ1800 ክፍለ ዘመን የተነገረ ወይም የተሰጠ መልእክት አሁን ባለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ማዋል እንችላለን ብለን እንጠይቃለን? አጠቃላይ የትንቢት መንፈስን ፅሁፍ ስናነብ በዚያን ጊዜ የተነገሩ መልዕክቶች ነበሩ እንዲሁም በአሁኑ ዘመን በትንቢት መልክ ተነግረው ያሉ ብዙ ትንቢተኞች አሉ።

‹‹ ተገልጾልኝ ነበር ከረጅም ጊዜ በፊት የተሰጡን መመሪያዎች (መልዕክቶች) በአሁኑም ጊዜ ላለነው ሰዎች በጣም አስፈላጊ እንደሆኑና አሁን ባለንበት ጊዜ እንደተሰጡን አድርገን ልንቀበላቸው ይገባል›› testimonies V.9 page 158

“እረጅም እድሜ ኖርኩኝ ወይም አጭር ዘመን የኔ ጽሁፎች ግን ሳያቋርጡ ይናገራሉ ስራውም እስከ መጨረሻ ዘመን ድረስ ይቀጥላል” Testimonies Page.13.14

የትንቢት መንፈስ ጽሁፎች አላማፋቸው ለአንድ ሰው እንኳን የተፃፈ ቢመስሉም ለብዙ ሰው የሚውል መልእክት በውስጣቸው ያለባቸው ናቸው ::

ለቤተክርስቲያን የተሰጠው ምክር በኤለን ጂ ዋይት አማካኝነት ሁሉም ነገር በተመሳሳይ ሁኔታ ለሁሉም ሰው ላይውል ይችላል፣ አለማቀፍ ይዘት ነው ያላቸው የኤለን ጂ ዋይት ጽሁፎች ልክ እንደ መፅሀፍ ቅዱስ አንድ አይነት አመራር ነው ያላቸው::

5. **ክፉውን ትቃወም ነበር**

‹‹ የኔ ስራ ስህተትን በመግለፅ ማሳወቅ (መናገር) ነው :: የአንዳንድ ሰዎች ጎጢያት በግልፅ ይታያል:: ጌታ አሳይቶኝ ነበር የኔ ምርጫ አይደለም ስራዬ ለመምረጥ ነገር ግን በትህትና እግዚአብሔርን መታዘዝ ነበር ... ›› PM 379 ‹‹ሁሉንም ነገር ፈትኑ በመልካሙ ተያዙ ይላል›› ጳውሎስ::

ለሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት አሁን ላለችበት ደረጃ እንድትደርስ የኤለን ጂ ዋይት ድርሻ በጣም ከፍተኛ ድርሻ ነበረው:: የትንቢት መንፈስን እግዚአብሔር መስጠቱ ምን ያህል በረከት እንደሆነ እናያለን፣ ኤለን ጂ ዋይት ለአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን አሁን የደረሰችበትን በትምህርት፣ በጤና፣ በወንጌል ስርጭት፣ በበጎ አድራጎት፣ ዓለም አቀፍ ደረጃን እንድትይዝ ቀዳሚ ሚና ተጫውታለች ::

ሌሎች የኤለን ጂ ዋይት ስራዎች

1. የቤተክርስቲያንን ዶክትሪን በማውጣት ለቤተክርስቲያን በጣም ትልቅ አስተዋፆኦ አድርጋለች::
2. ከአክራሪነት እና ከስህተት ትምህርት ቤተክርስቲያን እንድትጠበቅ እረድታለች::
3. ድርጅቱ እንዲቋቋም እረድታለች::
4. ወቅታዊ የሆኑ ችግሮችን በመፍታት እረድታለች::
5. የወደፊቱን እቅድ በማውጣት ትልቅ አስተዋፆኦ አድርጋለች::
6. ወደፊት የሚሆነውን ነገር ትናገራለች::
7. መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጠና በጣም አበረታታለች::
8. በጥሩ ክርስቲያናዊ ኑሮ በመኖር መርታ አሳይታለች::

ኤሌን ጂ ዋይት ፅሁፎች የተዘጋጁት በአራት መንገድ ነበር

1. Articles (አርቲክል) በፅሁፍ

‹‹የራሴ የሆነን አንድ አርቲክል እንኳን በወረቀት ላይ አልፃፍኩም፤ ሁሉም እግዚአብሔር በራዕይ ያሳየኝ ናቸው፡፡ ይህ የእውነት ብርሃን የመጣው ከእግዚአብሔር ዙፋን ስር ነው፡፡ በደብዳቤ መልክ የተዘጋጀ ነበር፡፡ ኤለን ጂ ዋይት ለብዙ ሰዎች በችግር ላይ ሲሆኑ ወይም በሌላ ምክንያት ብዙ ጊዜ ደብዳቤ ትጽፍላቸው ነበር፡፡

‹‹እየፈራሁ እየተንቀጠቀጥኩ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ላይ ተነስቼ ይሄንን ደብዳቤ የፃፍኩልሽ እግዚአብሔር በሽክላ እየተናገረ ነው ምን አልባት ይህ መልእክት የመጣው በደብዳቤ ነው ልትይ ትችያለሽ አዎን ደብዳቤ ነው ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ገፋፍቶኝ ነው ይህን ደብዳቤ የፃፍኩልሽ ልክ ጌታ እንዳሳየኝ ነው ››

የኤለን ጂ ዋይት የህይወቷ ታሪክ

አንድ በተለየ ቀን Dec.1844 ሄለን ሀርምን እና ሌሎች አድቬንቲስቶች ከእግዚአብሔር ነው ብለው የተቀበሉትን ራዕይ ተቀብላለች ‹‹በታያቸው ብርሃን የሚቀጥሉ ከሆነ (የሚራመዱ) ከሆነ እግዚአብሔር እንደሚመራቸው ታይታት ነበር›› ER P13-20

ሁለተኛ ራዕይ ‹‹እሷ ስለምታሳልፈው መከራ፤ እንዲሁም የእርሷን ልምምዶችም ለሌሎች እንደምትናገር ተነግሯት ነበር›› ሄለን ሀርምን ወጣት ነበረች ብዙ ጊዜ የሚያማት የሚደክማት እንዲሁም ብዙ ጊዜ ከሰዎች ጋር የማትደባለቅ ነበረች፡፡ እሷ የተሰጣትን ተልእኮ የምትፈጽመው አልመሰላትም ነበር፤ እግዚአብሔርን ለምና ነበር፡፡ ይህንን ሸክም እንዲያነሳላት፡፡ የሆነ ሆኖ ግን ይህ ሃላፊነት አለቀቃትም ነበር ‹‹የገለጥኩልሽን ለህዝቦቼ አስታውቂ የሚል ነበር የተሰጣት መልስ›› በመጨረሻም በጓደኞቿ ጸሎት ከራሷ በሆነ ውሳኔ የተሰጣትን ሃላፊነት ለመቀበል ወሰነች፡፡

August 30/1846 ሄለን ሀርምን ከአድቬንቲስት ሰባኪ ጋር በጋብቻ ተሳሰረች የባልዋ ስም ጀምስ ዋይት ይባል ነበር፡፡ በሚለራይት እንቅስቃሴ በጣም ትልቅ አስዋፅኦ ያደረገ ሰውም ነበር፡፡

ኤለን ከመንታ እህቷ ኤልዛቤት ጋር ኖቬምበር 26 1827 ከሮበርት እና ዮኒስ ሐርመን ተወለደች በቤተሰብ ውስጥ 8 ልጆች የነበሩ ሲሆን እቤታቸውም በጣም የሚያስደስት ቦታ

እና ሥራ የሞላበት ነበር። ቤተሰቦቿ ወደ ሰሜን አሜሪካ በመሄድ ኑሮአቸውን በዚያ አደረጉ የቦታው ስም ፖርትላንድ ይባል ነበር።

በልጅነቷ ቤተሰቦቿን ማለትም እናቷን እና አባቷን በጣም በስራ ትደግፋቸው ነበር። በ9 አመቷ ከትምህርት ቤት በምትመለስበት ሰዓት አንድ ቀን አብራት ከምትማር ጓደኛዋ በተወረወረ ድንጋይ በጣም ተጎዳች ለሦስት ሳምንት ይህል አይምሮዋን አታውቅም ነበር። በተወረወረው ድንጋይ አፍንጫዋ ተጎድቶ የነበረ ሲሆን ፊቷም በዚህ አደጋ ምክንያት ተበላሽቶ ነበር ። በዚህም ምክንያት ትምህርቷን ልታቋርጥ ተገዳለች።

በ1840 ኤለን ከቤተሰቦቿ ጋር የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን ካምፕ ሚቲንግ ይካፈሉ ነበር። ካምፕ ዶቪድ በሚባል ቦታ በ12 አመቷ ልቧን ለኢየሱስ ሰጠች ሰኔ 26 ቀን 1842 በራሷ ፍቃድ ተጠመቀች የሚቶዲስት ቤተክርስቲያን አባልም ሆነች።

ኤለን ጂ ዋይት ከ130 በላይ መፅሐፍቶችን ጽፋለች የእርሷ ጽሁፎች በአለም ላይ በብዛት ከሚተረጎሙ መፅሐፍቶች መካከል ይመደባሉ። ጽሑፎቿም ከ150 በላይ በሚሆኑ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል።

ኤለን ጂ ዋይት ከ1827-1915 በህይወቷ ዘመን ከ5000 በላይ አርቲክሎችን (ፅሁፎች) ጽፋለች በአሜሪካ ውስጥ በብዛት ከሚተረጎሙ መፅሐፍት መካከል የእርሷ መጽሐፎች ናቸው።

ኤለን ጂ ዋይት ጽሑፎች የሚያካትቱት ስለ ሀይማኖት ስለ ትምህርት፣ ማህበራዊ ግንኙነት፣ ወንጌል፣ ትንቢት፣ ስለ ህትመት፣ ስለ ምግብ ሳይንስ፣ ስለጤና ስራ እና ስለ አስተዳደር ነው።

የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የኤለን ጂ ዋይት ጽሁፎች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ በዚህ መጨረሻ ዘመን ለምንኖር ሰዎች ከእግዚአብሔር የተሰጡ መሆናቸውን ታምናለች። ያምናሉ። ከ7 ዓመቷ ጀምሮ እስከሞተችበት ዘመን ድረስ 2000 ራዕይ እና ህልም ተሰጥቷታል ።

የትንቢት መንፈስ ጽሁፎች መፅሐፍ ቅዱስን የሚተኩ አይደሉም። በአንድ መስመር ላይ የሚቀመጡ አይደሉም መፅሐፍ ቅዱስ ብቻ የእርሷ እና የሌሎች ሰዎችን ጽሁፎች የሚለኩበት የመለኪት መጽሐፍ ነው።

ማጠቃለያ

ይህ ፅሁፍ ከተለያዩ መጽሐፍት የተውጣጣ ሲሆን ቃል በቃል የተተረጎመ አይደለም ሀሳቡ ብቻ ተወስዶ የተተረጎመ ነው። በብዛት የተወሰደውም ነብያት በመካከላችን ከሚለው መሐሀፍ የተተረጎመ ነው።

ስለ ***<u>ኤሌን ጂ ዋይት (ስለ ትንቢት) መንፈስ ፅሁፎች ጥያቄ ያላችሁ ሰዎች ብታነቡት ትጠቀሙበታላችሁ።</u>***

_____//_____